# ክብረ ቅዱሳን የቅዱሳን ክብር ይህ መጽሐፍ

በቀሰሲ  ታደሰ አይፎክሩ የኢትዮጵያ  ኦርቶዶክስ
ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የሊቃውንት ጉባዔ አባል
እና የሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ
መንፈሳዊ ኮሌጅ
የሃይማኖት መምህር /ቲዎሎጂ/

በእግዚአብሔር ፈቃድ
በ2000 ዓ.ም
ለትምህርት ተዘጋጀ

# መውጫ


## መግቢያ

1. መቅም ክብረ ቅዱሳን
2. ምዕራፍ አንድ
ቅዱስ እግዚአብሔር በሥላሴነት
1. ምዕራፍ ሁለት
ቅዱሳን መላእክት እና ቅዱሳን የሰው ልጆች
ሀ. ቅዱሳን መላእክት
ለ. ቅዱሳን የሰው ልጆች
4. ሀ. የቅዱሳን መላእክት ስምና መገለጥ
5. ሊ. ቅዱሳን የሰው ልጆች
6. ምዕራፍ ሦስት
የቅዱሳን ቃልኪዳን
7. ምዕራፍ አራት
የቅዱሳን ክብር
ቁ.1 ቀደምት አበው
ቁ.2 ቅዱሳን ነቢያት
ቁ.3 ቅዱሳን አዋርያት
8. ለቅዱሳን ከእግዚአብሔር የተሰጠ ኃይል እና ሥልጣን
9. መ.ቅዱሰን ሰማዕታት
10. ሠ. ቅዱሳን ጻድቃን
ቁ.2 የጻድቃን መርህ የጻድቃን መመሪያ
11. ምዕራፍ አምስት
የቅዱሳን አማላጅነት
12. ምዕራፍ ስድስት
የቅዱሳን ምልጃ በብሉይ ኪዳን
13. ለ. በሐዲስ ኪዳን የቅዱሳን ምልጃ እና ዕርቅ አፈጻጸም
14 ሀ. በአጋንንት ላይ የተሰጠ ስልጣን
15. ለ. በደዌ ላይ የተሰጠ ስልጣን
16. ሐ. በሞት ላይ የተሰጠ ስልጣን
17. ምዕራፍ ሰባት
ሀ. የቅዱሳን መታሰቢያ በብሉይ ኪዳን መታሰቢያ
20. ምዕራፍ ስምንት
የጽሁፍ መጠቃለያ መልእክት
21. ማሳሰቢያ


# መቅድም

## ክብረ ቅዱሳን /የቅዱሳን ክብር/

ከሁሉ በፊት ቅዱስና ቅዱሳን የሚባሉት እነማን ናቸው? መልሱ ቅዱስ እግዚአብሔርና የቅድስና ስም ከፈጣሪያቸው የተ ሰጣቸው ቅዱሳን መላእክትና ምድራውያን ሰዎች ናቸው።

# ምዕራፍ 1

## ቅዱስ እግዚአብሔር በሥላሴነት

ቅዱስ፡- ቅዱስ ማለት ምን ማለት ነው? ቅዱስ ማለት ልዩ፣ ንፁህ ክቡር፣ ወዘተ ማለት ሲሆን ቅድስና ማለት ርኩሰት፣ ዝቅተኛነት ጉስቁልና፣ እድፈትና፣ ኃጢያት የሌለበት ሕይወት ማለት ነው። ይህ ዓይነቱ ሀብትነቱና ገንዘብነቱ በአንድ ባሕርይና በሦስት አካል የሚኖር የእግዚአብሔር አምላክ ብቻ ነው።

ቅዱስነት ለእግዚአብሔር በእራሱ ከእራሱ የተገኘ ከፍጡራን ያላገኘው ራሱን በእራሱ ለፍጡራን የሚገልጥበት የባህርዩ ልዩነትና የባህርዩ ክብር የባህርዩ ንፅሕና መገለጫና መጠሪያ ነው። ስለሆነም ቅዱስነት ለእግዚአብሔር የባህርይ ገንዘቡና ስሙ ነው። ለዚህም ከቅዱስ መጽሐፍ የሚከተሉትን ማስረጃ ዎች መመልከት ይበቃል፡-

1. ለዘለዓለም የሚኖር ስሙ ቅዱስ የሆነ ከፍ ያለው ልዑል እንዲህ ይላል። ትን ኢሳ.ምዕ.57 ቁ.15
2. እንግዲህ እተካከለው ዘንድ በማን መስላችሁኝ ይላል ቅዱሱ ትን. ኢሳ. ምዕ. 40ቁ.25
3. እሱ ራሱ እግዚአብሔር እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ! ዘ ሌ.ምዕ.19 ቁ.2፣ 1ኛ :ጴጥ.ምዕ.1 ቁ.15-16
4. ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ምድር ሁሉ ከክብሩ ተሞልታለች፡- ትን.ኢሳ. ምዕ.6ቁ.3

5. ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ የነበረውና የሚመጣው ሁሉንም የሚገዛ ጌታ ጌትነት ያለው አምላክ ራ.ዕ.ምዕ.4 ቁ.8
6. ድንግል ማርያምም ይህ ስም የማን እንደሆነ የእግዚአብሔር ስም እንደሆነ ስላወቀች ስሙም ቅዱስ ነው ብላለች:: ሉቃ ምዕ.1.ቁ48፣ መዝ.32 ቁ.21፣ መዝ.132 ቁ.2 ወዘተ

## ምዕራፍ 2

በፍጡራን ማዕከል ውስጥ የሚገኙ ቅዱሳን ሁለት ብቻ ናቸው:: እነሱም:-

ሀ. ቅዱሳን መላእክት እንደተፈጥሮአቸውና እንደስራቸው ከአምላካቸው የተሰጠ ስም ነው::

ለ. ቅዱሳን የሰው ልጆች እንደጥሪያቸውና እንደሥራቸው ከአምላካቸው የተሰጠ ስም ነው::

ሀ. ቅዱሳን መላእክት

ቅዱሳን መላእክት የፈጠራቸው የኃይል ባለቤት እግዚአብሔር በሥላሴነቱ መሆኑ ቢረጋገጥም የተፈጠሩበት ባህርያዊ ንጥረ ነገር በማስረዳትነት እስካሁን ድረስ የቀረበ ወይም የተጻፈ ነገር አለመገኘቱ እግዚአብሔርን ለጥያቄ የሚጋብዝ ሆኖ ይኖራል:: አንዳንድ ሥነ ጽሑፎች ለምሳሌ ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊትና እንደመቃብያን ያሉት ጽሑፎች ቅዱሳን መላእክት ከእሳትና ከነፋስ እንደተፈጠሩ ያመለክታሉ:-

1ኛ. መዝ.103/104/ቁ.4 ላይ መላእክቱን መንፈስ የሚያደርግ አገልጋዮቹንም የእሳት ነበልባል የሚለውን ዐረፍተ ነገርና ሐረግ በመከተል:-

2.ኛ መቃብያን ቀዳማዊ ምዕ.13 ቁ.15 ላይ ከእሳት ከነፋስ የፈጠራቸው እሱ እንደሆነ ስላወቁ እነሳቸው በተዋረደ ልቡና ፈጣሪያቸውን ያመስግኑታልና ከትዕዛዙም አይወጡምና... እንዳንተ ካሉ ከመላእክት ሁሉ ተለይተህ ተዋረድህ የሚለውን ዐረፍተነገርና ሐረግ



በመመልከት ቅዱሳን መላእክት ከእሳትና ከነፋስ እንደተፈጠሩ ይናገራሉ ይህ ስህተት ነው:: ብዙዎች የትርጓሜ ሊቃውንት ግን የእሳትና የነፋስ ስለቅዱሳን መላእክት በቅዱስ መጽሐፍ መጠቀሱ ለመላእክት ግብር /ሥራ/ በምሳሌነት ለመግለጽ የሚጠቅም እንጂ የቅዱሳን መላእክት ተፈጥሮ ከእሳትና ከነፋስ አይደለም:: እነሱ የተፈጠሩት በእግዚአብሔር ኃይልና ችሎታ እምኀበ አልቦ ኀበቦ ካለመኖር ወደ መኖር ያለምንም የፍጥረት ንጥረ ነገር ምክንያት በረቂቁ አለም በሰማይ የተፈጠሩ ረቂቃን ፍጥረቶች ናቸው:: እሳትና ነፋስ በምሳሌነት ለመላእክት የተጠቀሱት ኃይላቸውንና ፍጥረታቸውን ለመግለጽ ሲባል እንደሆነ መታወቅ አለበት:: ምክንያቱም እሳትና ነፋስ ሌሎችም ፍጥረታት የተፈጠሩባቸው ከአራቱ ባህርያት ከመሬት፣ ከውሃ ወገን ስለሆኑ ኃላፊያን ናቸው:: መላእክት ግን ኀልፈት ውላጤ /መለወጥ/ የለባቸውም ሕያዋን ፍጥረታት ናቸው:: ስለመላእክት ተፈጥሮ እውነቱ ይህ ብቻ ነው::

## የቅዱሳን መላእክት ስምና መገለጥ

የመላእክት ስማቸው ከሥራቸው የተወረሰ ነው:: በግእዙ ቋንቋ ለአከ ማለት ላከ ማለት ሲሆን መላእክት ማለትም በብዙ ሲተረጎም መላእክት መልእክተኞች ማለት ነው:: ይህ የወል /የጋራ/ ስማቸው ነው:: ሥራቸው ከእግዚአብሔር ወደ ሰው ከሰው ወደ እግዚአብሔር መላላክ ስለሆነ ነው:: የእያንዳንዱን መልአክ ስም ያወጣና ማን መሆኑንም የገለጠ የለም:: ስማቸውን የገለጡ ራሳቸውና ራሳቸውንም የገለጣቸው የፈጠራቸው አምላክ እግዚአብሔር ብቻ ነው::

ቅዱሳን መላእክት የእግዚአብሔር የኃይሉ መገለጫዎች ናቸው:-

ሀ. ከእሱ ጋር በአምልኮ ለሚኖሩ የምህረቱ

ሰ. ከእሱ ጋር በአምልኮ ለማይኖሩ የቅጣቱ መሳሪያዎች ናቸው:: ሮሜ ምዕ 9-22 ቁ.23

1. ለምህረት ሲላኩና ሲገለጡ:- ዘካ.ምዕ.1 ቁ.12 ሉቃ.ምዕ.2 ቁ.10 ዕ ብ .ምዕ.1 ቁ.14 ወዘተ መመልከት ይቻላል::
2. ለቅጣት ሲላኩና ሲገለጡ:- ኦሪ.ዘፀ.ምዕ.23 ቁ.20-21 የሐዋ.ሥራ ምዕ.12 ቁ.23 ወዘተ መመልከት ይቻላል::

ቅዱሳን መላእክት በቦታም ሆነ በተፈጥሮ ከሰው ቦታና ፍጥረት /አፈጣጠር/ የተለዩ ናቸው:: ለፍጥረት ሲገለጡም በፈለጉትና በፈለጋቸው መልክ ፈጣሪያቸው ይገልጣቸዋል እንጂ እንደሰው የተለያየ መልክ ያላቸው አይደለም እስካሁን ድረስ ስማቸውን ለሰው የገለጡትና በሥራ የተገለጡ ጥቂቶች ናቸው:: ለምሳሌ:- ቅዱስ ሚካኤል፣ ቅዱስ ገብርኤል፣ ቅዱስ ሩፋኤል፣ ቅዱስ ራጉኤል፣ ቅዱስ ዑራኤል፣ ቅዱስ ራሙኤል፣ ቅዱስ ፋኑኤል፣ ቅዱስ ሳቁኤል፣ ቅዱስ አፍኒን ወዘተ ናቸው:: ኢሳ.ምዕ.6 ቁ.2 ሕዝ.ምዕ.1 ቁ.6ዳን.ምዕ.9 ቁ.21 ምዕ.10 ቁ.13 እና 21 የይሁዳ መል.ምዕ 1 ቁ.14 ተመልከት::

ቅዱሳን መላእክት ቅዱስና ቅዱሳን ተብለው የሚጠሩት በፍጥረታቸው ልዩነትና ሥራቸው ለሌሎች ፍጥረታት የተለየና ባሕርያቸው እንደፈጠራቸው እንደ እግዚአብሔር ሕያውነት የተመላ ከማናቸውም ፍጡራን የተለየ የልዩ ቅዱስ እግዚአብሔር ተጠሪዎች ሥራ አስፈፃሚዎች ስለሆኑ በኑሮአቸው ለማያውያን በሥራቸው ምድራውያን ሰዎችን ከሰይጣን የሚታደጉ እንደሆኑ ቅዱሳት መጽሐፍት በሰፊው ይገልፃሉ:: ቅዱሳን መላእክትን ከቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ እግዚአብሄርን ከቅዱሳን መላእክት ለይቶ መናገር ስህተት ነው:: የባህርዩ የፈቃዱና የኃይሉ መገለጫዎች ስለሆኑ በመሆኑም ቅዱሳን መላእክት ለሰው ልጆች የቅርብ ረዳቶችና አጋሮች ስለሆኑ ልዩ የሆነ ክብር አላቸው:: ስማቸው ለመታሰቢያነት በጽላት ሕግ ላይ የሚቀረፀው ከዚህ በመነሳትና እግዚአብሔርም እሱ በሚመለክበት ቦታ ሁሉ ስማቸው እንዲጠራና ሥራቸው እንዲገለጥ ስለፈቀደ ነው::



ሔኖክ ምዕ.6 ቁ.1-8 ምዕ.10 ቁ12-16 ዘፀ.ምዕ.23 ቁ20-23 ኢያሱ ምዕ.5 ቁ.13-15 መዝ 33 ቁ.7 ሐ.ሥራ ምዕ.12 ቁ.23 ኦሪት ዘፍ.ምዕ.19-22 ወዘተ.

ስለዚህ ቅዱሳን መላእክት በሰው ዘንድ ባህርያቸው በማይፈቅድላቸውና ከአምላካቸው ባልተፈቀደላቸው የማይመለኩና ባህርያቸውና ሥራቸው በሚፈቅድላቸው የሚፈሩና የሚከበሩ ቅዱሳን ናቸው:: ይህም ክብር የሰው ልጅ በምድራዊ ህይወት እስካለ ድረስ የሚቋረጥ አይደለም:: የቅዱሳን መላእክት ህይወትና ሥራ በአጭሩ ከላይ የተጠቀሰውን ይመስላል::

ለ. <u>ቅዱሳን የሰው ልጆች</u>

የሰው ልጆች እንደጥሪያቸውና እንደሥራቸው ከፈጣሪ ከእግዚአብሔር ቅዱስና ቅዱሳን ብፁዕና ብፁዓን በሚል ስም እንዲጠሩ ተፈቅዶላቸዋል ለማስረጃም ያህል የሚከተሉትን አምላካዊ (ድምፆች) ቃሎች መመልከት ይቻላል::

1. ኩኑ ቅዱሳን እስመ አነ ቅዱስ እኔ ቅዱስ እንደሆንኩ እናንተም ቅዱሳን ሁኑ:: ዘሌ.ምዕ.19 ቁ.2 ምዕ.11 ቁ.44 1ኛ ጴ ጥ.ምዕ.1 ቁ.15-16
2. ቀደስኩከ እምከርሰ እምከ ከኅማፀንም ሳትወጣ ቀድሼሃለሁ:: ኤር.ምዕ.1 ቁ.4-5ዮሐ.ምዕ.17 ቁ.17-19 ራዕይምዕ.8 ቁ.4 1ኛ ቆሮ.ምዕ.3 ቁ.16-17 ወዘተ
3. በክርስቶስ አምነው የተጠመቁ ሰዎች ብፁዓን ተብለውእንዲጠሩም ተፈቅዶላቸዋል:: ለምሳሌ:- በመንፈስ ድሆች የሆኑ ብፁዓን ናቸው ማቴ.ምዕ.5 ቁ.1-15 ምዕ.16 ቁ.17 እነዚህ ከዚህ በላይ ቅዱስና ብፁዕ የተሰኙ ቃላት ከእግዚአብሔር የተነገሩት እንዲያው አይደለም:: ለአምላካዊ ሥራ ራሳቸውን ለዓለም ክብርና ጣዕም 1ኛ በጥምቀት 2ኛ በሥራ 3ኛ በኍመት ሕይወታቸውን

ለአምላክና ለመንግስተ ሰማይ ለሰጡ ሰዎች የተሰጠ ስም ነው:: እነዚህም እንደየወገናቸው የሚከተሉት ናቸው:-

ሀ. ቅዱሳን ቀደምት አበው:- እንደጥሪያቸውና እንደሥራቸው በእግዚአብሔር የተመረጡ

ለ. ቅዱሳን ነቢያት:- እንደጥሪያቸውና እንደሥራቸው በእግዚአብሔር የተመረጡ

ሐ. ቅዱሳን ሐዋርያት:- እንደጥሪያቸውና እንደሥራቸው በእግዚአብሔር የተመረጡ

መ. ቅዱሳን ሰማዕታት:- እንደጥሪያቸውና እንደሥራቸው በእግዚአብሔር የተመረጡ

ሠ. ቅዱሳን ጻድቃን:- እንደጥሪያቸውና እንደሥራቸው በእግዚአብሔር የተመረጡ ናቸው::

እነዚህ ከላይ ከተራ፡ ፊደል ሀ እስከ ተራ ፊደል ሠ ድረስ በየወገናቸው በጥቅል የተመዘገቡ:- አበው ቅዱሳን አበው ነቢያት፣ ሐዋሪያት፣ ሰማዕታት፣ ፃድቃን፣ ብፁዓን፣ ተብለው እንዲጠሩ እግዚአብሔር ያደላቸውና የፈቀደላቸው የእግዚአብሔ ር ሰዎች አባቶች እሱ ራሱ እግዚአብሔር የመረጣቸው ለሥራ የጠራቸው ራሱን የገለጠላቸው በእነሱ ለሌላው እንዲገለጥ የፈቀደላቸው በቤተ መቅደሱም ሰማቸው ከእርሱ ጋር እንዲጠራ የፈቀደላቸው ከሁሉም በላይ እሱን ወክለው የማዳንና የማስታረቅ ሥራ እንዲሰሩ ሥልጣን የሰጣቸው የሃይማኖት ዕንቁና የራሱ የእግዚአብሔር የፀጋው ልጆች ናቸው::

ለዚህም ነው ነቢዩ ኢሳያስና ቅዱስ ጳውሎስ በትንቢታቸውና በመልክታቸው እንዲህ ሲሉ የፃፉት ደስ የሚያሰኘኝንም ነገር ስለሚመርጡ ቃል ኪዳኔንም ለሚይዙ ጃንደረቦች በቤቴና በቅጥሬ ውስጥ ከወንዶች ልጆችና ከሴቶች ልጆች ይልቅ የሚበልጥ መታሰቢያና ስም እሰጣቸዋለሁ:: የማይጠፋም የዘለዓለም ስም እሰጣቸዋለሁ ሲል የተናገረው ትን.ኢሳ.ምዕ.56 ቁ.4-8 ተመልከት::

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ለእነዚህ የእግዚአብሔር ሰዎች ሲጽፍ እንዲህ ብሏል::



እግዚአብሔር ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ በብዙ ወንድሞቹ መካከል በኩር ይሆን ዘንድ አስቀድሞ ያወቃቸውን የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ወስኗልና አስቀድሞ የወሰናቸውን እነዚህን ደግሞ ጠራቸው የጠራቸውንም እነዚህን ደግሞ አጸደቃቸው የጸደቃቸውንም እነዚህን ደግሞ አከበራቸው ያለው ሮሜ ምዕ.8 ቁ.29-30 ተመልከት::

# ምዕራፍ 3

## የቅዱሳን ቃል ኪዳን

እግዚአብሔር በሥላሴነቱ ለምህረት፣ ለይቅርታ፣ ለድኅነት ቃል ኪዳን /ውል/የገባላቸው ቅዱሳን የሚከተሉት ናቸው:-

ሀ. ቀደምት አበው እንደእምነታቸውና እንደሥራቸው

ለ. ነቢያት እንደእምነታቸውና እንደሥራቸው

ሐ. ሐዋርያት እንደእምነታቸውና እንደሥራቸው

መ. ሰማዕታት እንደእምነታቸውና እንደሥራቸው

ሠ. ፃድቃን እንደእምነታቸውና እንደሥራቸው

እነዚህ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ቅዱሳን እግዚአብሔር ለማዳን ሥራው የጠራቸውና በእሱና በሰው መካከል ቆመው የማማለድና የማስታረቅ ሥራ እንዲሠሩ በእሱ በራሱ በእግዚአብሔር የተመረጡ ናቸው:: እነዚህ ቅዱሳን በተ ገባላቸው ቃል ኪዳን መሰረት በእግዚአብሔር የተመረጡ ናቸው:: እነዚህ ቅዱሳን በተገባላቸው ቃል ኪዳን መሠረት በዓለመ ሥጋ በነበሩበትም ጊዜ አሁንም በአፀደ ነፍስ ባሉበት ጊዜ ሁሉ የዓለም ፍፃሜ /ኅልፈተ ዓለም/ እስከሚፈጸም ድረስ የማማለድና የማስታረቅ ስራቸው አይቋረጥም ሞት /ሞተ ሥጋ/ በሐዲስ ኪዳን ትምህርት የቦታ መቀየሪያ የህይወት መለወጫ እንጂ የህይወት ፍፃሜ ስላልሆነ ነው:: እንዲህም በመሆኑ የሰው ልጆች ሕይወት ስለማይቋረጥ የቅዱሳንም ሥራ እስከ ኅልፈተ ዓለም አይቋረጥም ::ክርስቶስም ሰው የሆነበት ዋናው ዓላማ ይኸው ነውና:: ለቅዱሳን ቃል ኪዳንም ሊገባ

የቻለው ለማይቋረጥ ለሰው ልጆች ህይወት ነው::

## ቃል ኪዳኑም:-

1. ኪዳነ ተካየድኩ ምስለ ኅሩያንየ ወመሃልኩ ለዳዊት ገብርዩ ከመረጥኩት ጋር ቃል ኪዳኔን አደርጋለሁ ለባሪያዬም ለዳዊት ማልሁ:- መዝ88/89/ቁ.3
2. ለዘለዓለም ምህረቴን ለእርሱ እጠብቃለሁ ኪዳኔም በእርሱ ዘንድ የታመነ ነው:: መዝ.88/89/ቁ.28-34
3. እግዚአብሔር ለኖኅና ለልጆቹ እንዲህ ብሎ ተናገረ እነሆ ቃል ኪዳኔን ከእናንተና ከእናንተ በኋላ ከሚመጣው ከዘራችሁ ጋር አቆማለሁ:: ዘፍ.ምዕ9 ቁ.8-17
4. እርሱ አምላክ እንደሆነ ለሚወዱትም ትእዛዙንም ለሚጠብቁ ቃል ኪዳኑንና ምህረቱን እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ የሚጠብቅ የታመነ አምላክ እንደሆነ እወቅ ዘዳ.ምዕ.7 ቁ.9-11
5. እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል እኔንም የሚቀበል የላከኝን ይቀበላል:: ነቢይን በነቢይ ስም የሚቀበል የነቢይን ዋጋ ይወስዳል:: ጻድቅንም በጻድቅ ስም የሚቀበል የጻድቁን ዋጋ ይወስዳል ማንም ከእነዚህ ከታናናሾቹ ለአንዱ ቀዝቃዛ ጽዋ ውሃ ብቻ በደቀ መዝሙር ስም የሚያጠጣ እውነት እላችኋለሁ ዋጋው አይጠፋበትም:: ማቴ.ምዕ.10ቁ.40-42 ማር.ምዕ9 ቁ.41 ሉቃ.ምዕ.10 ቁ.16
6. ነህምያም አቤቱ የሰማይ አምላክ ሆይ ለሚወዱህና ትዕዛዝህን ለሚጠብቁ /ለሚያደርጉ/ ቃል ኪዳንንና ምህረትን የምትጠብቅ ታላቅ የተፈራህ አምላክ ሆይ ስለእስራኤል የምጸልየውን ጸሎት ስማ ብሏል::ነህምያ ምዕ.1 ቁ.5-6 ተመልከት:: ባጭሩ ከላይ የተጠቀሱት ቃላት እግዚአብሔር ለቅዱሳን የገባላቸው ቃል ኪዳን /ውል/ ያመለክታሉ ቅዱስ እግዚአብሔር ለቅዱሳን የሰጠውን ቃል ኪዳን እውን እንደሚያደርገውም የታመነ ነው እውነት እላችኋለሁ ሰማይና ምድር ያልፋሉ ቃሌ ግን አያልፍም ሲል አረጋግጧልና:: ማቴ.ምዕ.24 ቁ.34 ሉቃ.ምዕ.16 ቁ.17



አምላካችን እግዚአብሔር ቃሉን አይለውጥም እግዚአብሔር እንደ ፍጡር ባህርዩ አይለወጥም ሕዝ.ምዕ.12 ቁ.25 ሁሉም ነገር በእርሱ ዘንድ እውነት ነው ይፈፀማል አይቀርም::

## ምዕራፍ 4

## <u>የቅዱሳን ክብር</u>

ከሰው ወገን ሰው ሆነው ተፈጥረው ቅዱስና ቅዱሳን በሚለው ስም ለመጠራት የበቁና የሚጠሩ ሰዎች ያለምንም ከምንም ተነስተው አይደለም ስሙንም የተጠሩበትና ያገኙት ከራሳቸውና ከሰው አይደለም ከእምነታቸውና ከዓላማቸው ፅናት የተነሳ ከፈጣሪያቸው በፀጋ የተሰጣቸው ስም ነው::

በእነዚህም ስም ለመጠራት መነሻ የሆናቸው:-

1ኛ. ወምንተ ይበቁዖ ለሰብእ ለእመ ኩሎ ዓለም ረብሃ ወነፍሶ ሃጉለ:- ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ/ገንዘብ/ቢያደርግ ነፍሱንም ቢያጎድል ምን ይጠቅመዋል?

2ኛ. ወዘይፈቅድ ያድኅና ለነፍሱ ለይግድፋ ወዘሰ ገደፋ ለነፍሱ በእንቲአየ ይረክባ ነፍሱን ሊያድን የሚወድ ሁሉ ያጠፋታል ስለእኔ ግን ነፍሱን የሚያጠፋ ሁሉ ያገኛታል/ያድናታል/::

3ኛ. ዘይፈቅድ ይትልወኒ ይጽልአ ለነፍሱ ወይጥብዕ ወይንሣእ መስቀለ ሞቱ ወይትልወኒ እኔን መከተል የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ መስቀልንም/መከራንም/ ገንዘብ አድርጎ ይከተለኝ/ ይምሰለኝ/ ማቴ.ምዕ.16 ቁ.24-26 ወዘተ

4ኛ. ባኡ እንተ ጸባብ አንቀጽ እስመ ረሃብ አንቀጽ ትወስድ ውስተ ኃጉል ወብዙኃን ይበውኡ ውስቴታ ጥቀ ጸባብ አንቀጽ ወጽዕቅት ፍንኖት እንተ ትውስድ ውሰተ ሕይወት ወውኅዳን እሙንቱ እለይበውእዋ በጠበበው ደጅ ግቡ ወደ ጥፋት የሚወስደው ደጅ ሰፊ መንገዱም ትልቅ ነውና ወደእርሱ የሚገቡ ብዙዎች ናቸው ወደ ህይወት የሚወስደው ደጅ ግን የጠበበ ምንገዱም የቀጠነ ነውና የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸው:: ማቴ.ምዕ.7 ቁ.13-14 ትርጉሙም ባጭሩ የክርስትና ህይወትና ክርስቶስን በሥራ መምሰል ነው::

5ኛ.ዘያፈቅር አባሁ ወእሞ እምኔየ ኢይደሉ ሊተ ወኢይክል ይጸመደኒ ወዘያፈቅር ወልዶ ወወለቶ እምኔየ ኢይደሉ ሊተ ወኢይክል ይጸመደኒ:-ከእኔ ይልቅ አባቱን ወይም እናቱን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባውም ከእኔ ይልቅም ወንድ ልጁን ወይም ሴት ልጁን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባውም በማለት የተሰጠውን አምላካዊ ቃልና መመሪያበመከተል

6ኛ. እስመኩሉ ዘሀሎ ውስተ ዓለም ፍትወቱ ለሥጋ ወፍትወቱ ለዓይን ወሥራሁ ለመንበርት ኢኮነ ዝንቱ እምሃበ አብአላ እምዓለም ውእቱ ዓለሙኒ የኃልፍ ወፍትወቱኒ የኃልፍ ወዘሰ ይገብር ፍትዎቶ ለእግዚአብሔር ይነብር ለዓለም ዓለምን ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ በዓለም ያለው ሁሉ እርሱም የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት እንጂ ከእግዚአብሔር አብ ስላልሆነ ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት የእግዚአብሔር ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም:: ዓለሙም ምኞቱም ያልፋሉ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ግን ለዘለዓለም ይኖራል:: 1ኛ ዮሐ.ምዕ2ቁ.16-17የሚለውን ሐዋርያዊ መመሪያ በመከተል

7ኛ. ወባሕቱ በከመ ዘጸወዐክሙ ቅዱስ ውእቱ አንትሙኒ ኩኑ ቅዱሳነ በኩሉ ግእዝክሙ:- የጠራችሁ ቅዱስ እንደሆነ እናንተም ደግሞ በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ:: 1ኛ ጴጥ.ምዕ.1 ቁ.15-16

8ኛ. የተጠራችሁለት ለዚህ ነውና ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌ ትቶላችሁ ስለእናንተ መከራን ተቀብሏልና:: 1ኛ ጴጥ ምዕ.2 ቁ.22-23 ወዘተ የሚለውን ሐዋርያዊ ቃልና መመሪያ በመከተል እንደምርጫቸው ቃሉን ተግባራዊ በማድረጋቸው ለክርስትና ሕይወት እውነትነትና ለአምላካቸው ሥራ ብቁና ምስክር ሆነው በመገኘታቸው ቅዱስና ቅዱሳን ተብለው በዚህ ስም እንዲጠሩ ለቅድስና ሥራ የጠራቸው አምላካቸው ፈቅዶላቸዋል::

## የቅዱሳንስምና ክብር በእግዚአብሔር ዘንድ

ቅዱሳን ተብለው የሚጠሩ የሰው ልጆች ይህን ስም ያገኙት እግዚአብሔር ለማዳን ሥራው የጠራቸውና የመረጣቸው



በጥሪያቸው መሠረት ራሳቸውን በእግዚአብሔር ሥራ የገለጡና ያስመሰከሩ አጠቃላይ ምድራዊ የቅድስና ሕይወታቸው የመሰከረላቸው የሃይማኖትና የመልካም ሥነ-ምግባር አባቶች ናቸው:: እነሱም እንደቅደም ተከተላቸው የሚከተሉት ናቸው::

1ኛ <u>ቀደምት አበው</u>

1.1 <u>ሄኖክ ወልደ ያሬድ</u>:- ይህ ሰው የሰውን ተፈጥሮ ደካማነትና ምድራዊ ሕይወትም ከንቱ እንደሆነ በማሰብ ምርጫውን በመንፈሳዊ ሕይወት ለመምራት እግዚአብሔርን በአምልኮ ለመከተል የወሰነ እግዚአብሔርም ዓላማውን የተቀበለለት እንደሆነ እስከ አሁን ድረስ በሰው ላይ የተፈረደ መራራ ሞትን ሳይቀምስ በብሔረ ሕያዋን የሚገኝ ታላቅ የምናኔ አባት ለመሆኑ ቅዱስ መጽሐፍ ሄኖክም አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ በማለት መስክሮለታል:: ኦሪ.ዘፍ.ምዕ.5 ቁ.18-22 የይሁዳ መል.ምዕ.1 ቁ.14-15 ዕብ.ምዕ.11 ቁ.5-6 ወዘተ

1.2 <u>ኖኅ ወልደ ላሜህ</u>:- ይህ ጻድቅ አባት ምድር በሰው ልጆች አለመታዘዝ በኃጢአት በተበከለች ጊዜ እግዚአብሔርም በሰጠው ፀጋና ነፃ ፈቃድ ሰው መጠቀም አቅቶት በኃጢአት በመውደቁና ከፈጠረው አምላክ በመለየቱ ሰውን በምድር ላይ በመፍጠሩ በተጸጸተ ጊዜ ምድርንም በሰው ኃጢአት በንፍር ውሃ ባጠፋበት ጊዜ የእግዚአብሔር ምርጥ ሰው ሆኖ የተገኘ ታላቅ ጻድቅ አባት ነው::ይህ ታላቅ ጻድቅ አባት በመጀመሪያም በእናቱ ማኅፀን ሲፈጠር በእግዚአብሔር ለመልካም ሥራ የተመረጠ ለመሆኑ ቅዱስ መጽሐፍ መስክሮለታል እንዲህ በማለት ማቱሳላ ልጁ ላሜህን ሚስት አጋባው ከሱም ፀንሳ ወንድ ልጅ ወለደች የተወለደው ልጅም ሰውነቱ እንደ ዕንቁ ነጭ ሆነ እንደጽጌሬዳም ቀይ ነው ዓይኖቹንም በገለጠ ጊዜ ቤቱ ሁሉ እንደፀሐይ አበራ ከወላጂቱም እጅ በተነሳ ጊዜ ነገር ጀመረ የቸርነት ጌታ የእግዚአብሔርን ምስጋና ተናገረ ከዚህም የተነሳ አባቱ ላሜህ ፈርቶ ሸሸ ወደ አባቱም ወደ ማቱሳላ ሄዶ እኔ ልውጥ ልጅ ወሰድሁ እንደ ሰው አይደለም የሰማይ መላእክትን ይመስላል ፍጥረቱ ልዩ ናት አለው አባቱም ለልጁ

ለላሜህ ነገረው እሱ ከጥፋት የቀረ ይሆንላችኋልና ስሙንም ኖኅ ብለህ ጥራው ብሎ ቅድስናውን አያቱ ማቱሳላ መስክሮለታል:: ሄኖክ ምዕ.41 ቁ.17-20 ተመልከት:: ገና ሲወለድ ብርሃን የተሳለበትና እግዚአብሔርን ያመሰገነ ኖኅ በእግዚአብሔር ፊት ሞገስን አገኘ ኖኅም በትውልዱ ጻድቅ ፍጹምም ሰው ነበር ኖኅም አካሄዱን ከእግዚአብሔርም ጋር አደረገ:: ኦሪ.ዘፍ.ምዕ.6 ቁ.8-9 በማለት የተመሰከረለት ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር የማገናኘት ሥልጣን የተሰጠው የእግዚአብሔር ባለሟል እንደነበርና እግዚአብሔር ያነጋግረው እንደነበር በግልጽ ተጽፎ ይነበባል ይህም የቅዱሳን ከእግዚአብሔር መመረጥና ክብራቸው ምን ኃይል እንዳለው ይመሰክራል::

1.3 <u>አብርሃም ወልደ ታራ</u>:- አበ ብዙኃን /የብዙዎች አባት/ የሆነው አብርሃም እግዚአብሔርን ለማምለክና ለመታዘዝ ዓላማና ፍላጎት የነበረው ታላቁ የሰው ልጆች የድኅነት በር አባት እንደነበር በቅዱስ መጽሐፍ በብዙ ቦታ ተመዝግቧል:: እግዚአብሔርም ለአብርሃም ተገለጠለትና ይህችን ምድር ለዘርህ እሰጣለሁ በማለት ቃል ኪዳን የተገባለት ታላቅ ጻድቅ አባት እንደነበር ተመስክሮለታል:: ኦሪ.ዘፍ.ምዕ.12 ቁ.1-7 እንዲሁም ልዩ የእግዚአብሔር የድኅነ/የማዳን/ መሣሪያ ሆኖ በእግዚአብሔር አምላክ ስለተመረጠ በእግዚአብሔር ህያው ቃል ከአገርህ ከዘመዶችህም ከአባትህም ቤት ተለይተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር ውጣ! ታላቅ ህዝብም አደርግሃለሁ እባርክሃለሁ ስምህንም አከብርዋለሁ ለበረከትም ሁን! የሚባርኩንም እባርካለሁ የሚረግሙህንም ረግማለሁ የምድር ነገዶችም ሁሉ በአንተ ይባረካሉ ተብሎ የተመሰከረለት የምናኔና የቅዱሳን አባት ቅዱስ ለመሆኑና እግዚአብሄር የሰው ልጅ በኃጢአት ያጣውን ሕይወት ለመመለስ ሰው በሚሆንበት ጊዜ የመረጠው የድኅነት የዘር ሐረግ አባት መሆኑ በቅዱስ መጽሐፍ በስፋት ተረጋግጧል:: ኦሪ.ዘፍ.ምዕ12 ቁ.1-3 ምዕ.22 ቁ15-19 ማቴ.ምዕ.1 ቁ.1-25 ሮሜ.ምዕ.9 ቁ.4-5 ገላ.ምዕ.3 ቁ.6-7 ያዕ.2 ቁ.21::



አበ ብዙኃን አብርሃም የአምልኮና የሥነ-ምግባር ምንጭ ከመሆኑም በላይ የእግዚአብሔር የማዳን ሥራው መነሻና መድረሻ የሚስጥረ ሥጋዌ መገለጫ አባት ስላደረገው ትውልድ ሁሉ ሲያከብረውና በስሙ ሲማለድበት ይኖራል ስለሆነም በአጭሩ አብርሃም በእግዚአብሔር የተመረጠና የተከበረ አባት ስለሆነ በልጆቹ እንደተከበረ ዘለዓለም ይኖራል::

1.4 <u>ሙሴ ወልደ እንበረም</u>:- እግዚአብሔር ለታላቅ ዓላማና ሥራ የመረጠው ሙሴ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ3844 ዓ.ዓ ተወለደ ይህ የእግዚአብሔር ምርጥና መልእክተኛ ሙሴ የእግዚአብሔር መልአክ በእሳት ነበልባል በእሾህ ቁጥቋጦ መካከል እሳቱ ቁጥቋጦውን ሳያቃጥለው ቁጥቁጡ እሳቱን ሳያጠፋው የታየው እግዚአብሔር በኋላ ዘመን የሚያደርገውን ታላቅ ምሥጢር የገለጠለት የግብፅን ንጉሥ ፈርዖንን በ10 መቅሰፍት የቀጣና ወገኖቹ እሥራኤላውያንን በ3955 ዓ.ዓ ከግብፅውያን ባርነት በእግዚአብሔር ኃይል ነፃ ያወጣ የእግዚአብሔር ወገን ነገደ አብርሃም የሆኑትን እሥራኤላውያንን ለመምራትና ወደ ምድረርስትም ለማስገባት ሀብተ ክህነቶንና ሀብተ ምሥፍናን ሀብተ ትንቢትንም ከእግዚአብሔር የተሰጠው ታላቅ የሃይማኖት አባትና ታማኝ የሕዝብ መሪ ነበር:: ኦሪ.ዘጸ.ምዕ.3ቁ.2-15 ምዕ.12 ቁ.6-8 ከዚህም ሌላ ሕዝቡን የሚመራበት ሕገ እግዚአብሔር አሥርቱ ቃለተ ኦሪት በደብረ ሲና የተሰጠው ዘወትር እግዚአብሔር ቃል በቃል የሚያነጋግረው በፊቱ ላይ ብርሃን የተሳለበት ልዩ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ነበር:: ኦሪ.ዘጸ.ምዕ.3 ቁ.13-15 ምዕ.33 ቁ.17-23 ዕብ.ምዕ.3 ቁ.2ና5 ወዘተ ተመልከት:: ይህም ታላቅ ዓላማና ሥራው ከእግዚአብሔርም ጋር ያለው ግንኙነትና ታማኝነት እስከ ዓለም ፍፃሜ ድረስ በክብር ሲወሳና ሲነገር ይኖራል::

1.5 <u>ኢያሱ ወልደ ነዌ</u>:- ነቢየ ያነስእለክሙ እግዚአብሔር እምአኀዊክሙ ዘከማየ ወሎቱ ስምዕዎ ከወንድሞቻችሁ እንደ እኔ ያለ ነቢይ እግዚአብሔር ያስነሳላችኋል እርሱን ስሙት ተብሎ የተነገረለት ከሙሴ ቀጥሎ ሕዝበ እግዚአብሔር እሥራኤልን በክህነትና በምስፍና እየመራ /እያስተዳደረ/የታላቁን ወንዝ

የዮርዳኖስን ሙላት በእምነት ኃይል በማቆም ወደ ምድ ረ ርስትከነዓን ያስገባ ታላቅ የህዝብና የሃይማኖት መሪ /አስተዳዳሪ/ ኢያሱ ነበር:: ዘዳ.ምዕ18 ቁ.15-16 ምዕ.34 ቁ.8-9 መጽሐፈ ኢያሱ ምዕ.3 ቁ.8-17 ወዘተ ታላቁ የእግዚአብሔር ተወካይ ኢያሱ ህዝበ እግዚአብሔር እሥራኤልን በክህነትና በምሥፍና እንዲመራ የወከለው እግዚአብሔር በሕይወትህ ዕድሜ ሁሉ ማንም አይቋቋምህም ከሙሴ ጋር እንደነበርሁ እንዲሁ ከአንተ ጋር እሆናለሁ አልጥልህም አልተውህም ለአባቶቻችሁ እሰጣችኋ ለሁ ብዬ የማልሁላቸውን ምድረ ርስት ለዚህ ህዝብ ታወርሳለህና ጽና! አይዞህ እትፍራ!አገልጋዬ ሙሴ ያዘዘህን ሕግ ሁሉ ጠብቅ አድርገውም በምትሄድበትም ሁሉ ሥራህ እንዲከናወንልህ ወደ ቀኝም ወደ ግራም አትበል:: የዚህ ሕግ መጽሐፍ ከአፍህ አይለይ በቀንም በሌሊትም አሰበው ያን ጊዜ መንገድህ የቀናልሃል ይከናወንልሃልም በምትሄድበት ሁሉ አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነውና ጽና! አይዞህ አትፍራ ተብሎ ከፈጣሪው የማጽናኛ ቃል የተነገረለት ታላቅ የህዝብ መሪና ካህን ነበር:: ኢያሱም ይህን አምላካዊ ሥልጣንና አደራ ተቀብሎ ሳይፈራና ሳይጠራጠር ኃላፊነቱን በትክክል የተወጣ ይህዝብ መሪና የሃይማኖት አባት ነበር:: መጽ.ኢያሱ.ምዕ.1 ቁ.5-9 ምዕ.7 ቁ.6-26:: ይህ በእምነቱ ቆራጥና የእግዚአብሔር ታማኝ መሪ ኢያሱ እራሱ የሚመራቸው ሕዝቦች ከእግዚአብሔር አምልኮት ፈቀቅ ሲሉ ከእግዚአብሔር የተቀበለውን ኃላፊነት ለመወጣት ሲል ዕ ብራውያንን አሁንም እግዚአብሔር ፍሩ በፍጹምም ልብ አምልኩት አባቶቻችሁ በምድረ ግብጽ ያመለኳቸውን አማልክት /ጣዖታት/ ከእናንተ አርቁ:: እግዚአብሔርንም አምልኩ:: እግዚአብሔርንም ማምለክ ክፉ መስሎ ቢታያችሁ የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ! እኔና ቤቴ ግን የፈጠረንን አምላክ እግዚአብሔርን እናመልካለን በማለት ወሳኝ የሆነ አቋሙን ለሚመራው ህዝብ የገለጠ ሀቀኛ መሪ ነበር:: መጽሐፈ ኢያሱ ምዕ.24 ቁ.14-15 ተመልከት:: ከላይ በአጭሩ ሥራው



እንደተገለጸው ነቢየ እግዚአብሔር ኢያሱ በእግዚአብሔር የተ ጠራና የተመረጠ እምነቱንና ሥነ-ምግባሩን በትክክል የተወጣ እግዚአብሔር በእምነቱና በሥራው ውጤት ቃል በቃል ያነጋገ ረው የዮርዳኖስን ፈሳሽ ወንዝ እስከ ማቆምና አረማውያንን እስከ መቆጣጠር ከእግዚአብሔር ኃይልና ሥልጣን የተሰጠው ካህንና መስፍን ነበር:: እስካሁንም ድረስ ሥራው ለአማንያን አብነት ስለሆነ እንደ ሌሎች ቀደምት አባቶች ሲወሳና ሲከበር ይኖራል:: ቅዱሳን አባቶቻችንንም አማልክት ዘበፀጋ ሲያሰኛ ቸው የሚኖረው ኃይል ይኸው የሃይማኖታቸው ጽናትና የሥነ-ምግባራቸው ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ግንኙነትም ነው:: ስለሆነም ቅዱሳን አባቶችንን ከእግዚአብሔር እግዚአብሔርንም እሱ እራሱ ከመረጣቸው ቅዱሳን አባቶች መለየት አይቻልም ሥልጣንና ፈቃዱም የለም በዚህ ጉዳይ የሰው ልጆች ሊጠነቀቁ ይገባል:: እግዚአብሔር የመረጣቸውን ማን ይከሳል? ተብሎ ተ ጽፎአልና:: ሮሜ.ምዕ.8 ቁ.33 ኢሳ.ምዕ 50 ቁ.8-9 ተመልከት::

2ኛ <u>ቅዱሳን ነቢያት</u>

ቅዱሳን ነቢያት:- እንደእምነታቸው ጽናትና እንደሥራቸው ጥራት በእግዚአብሔር ለክብርና ለሕይወት የተመረጡ ለእግዚአብሔር የዓላማው የክብሩና የኃይሉ መልእክተኞችና የቅዱስ መንፈሱ መገለጫዎች የሚስጥረ ሥጋዌው መርሐ ግበር ቀያሾች ናቸው:: በመሆኑም ቅዱሳን ነቢያት ሀብተ ትንቢትና ሀብተ መንግስት ሀብተ ክህነትና ሀብተ መዊዕ ከእግዚአብሔር የተሰጣቸው የሕጉ ጠባቂዎችና አስከባሪዎች ከእግዚአብሔር ጋር ቃል በቃል በግልፅ የሚነጋገሩ የህዝበ እግዚአብሔር ማኅበረ ሰብእ ችግር ፈቺዎች እንደነበሩ የተቀደሰ ሥራቸው በቅዱስ መጽሐፍ በየስማቸው ተመዝግቦ እስከ ዓለም ፍጻሜ ለምስክርነት ሲነገር ይኖራል::

ከእነዚህም ቀደምት ነቢያት ለአብነት ያህል ዋና ዋናዎቹን በአጭሩ እንመልከት:-

2.1 <u>ነቢዩ ሳሙኤል ወልደ ሕልቃና :-</u> ይህ ነቢይ ዘመነ መሳፍንት አልፎ ዘመነ ነገሥት ሲተካ በቅዱስ

እግዚአብሔር ለተቀደሰ ክህነትና ለተቀደሰ ምስፍና ሥራ የተመረጠ ታላቅ የእግዚአብሔር ምርጥ ነው:: በተለይ እናቱ ሐና በብሉይ ኪዳን ከነበሩ ቅዱሳት ሴቶች በእምነትና በሥነ-ምግባር የፀናች በጸሎት ተወስና በቤተ እግዚአብሔር ተጠምዳ ትኖር የነበረች ቅድስት ናት:: ነቢዩ ሳሙኤልም የእናቱ የጸሎት ውጤት እንደነበር ቅዱስ መጽሐፍ ይገልጸዋል:: ቀዳ.ሳሙ.ምዕ1 ቁ.3 ና 21

ሳሙኤል ከሕፃንነቱ ጀምሮ በሊቀ ካህናቱ በኤሊ እግር ሥር ሕገ ኦሪትን ሲያጠና በቤተ መቅደስ ያደገ የእግዚአብሔርንም ድምፅ እየሰማ ለተቀደሰ ለክህነት ሥራ ሲዘጋጅ የነበረ ሰው ነው::

የሊቀ ካህናት የኤሊ ልጆች አፍኒንና ፊንሐስ በቤተ እግዚአብሔር የማይገባ ሥራ ሠርተው እግዚአብሔርን በማሳዘናቸው በእግዚአብሔር ከተቀጡ በኋላ ሳሙኤል በእነሱ እግር ተተክቶ ቤተ እግዚአብሔርን በቅዱስ የክህነት ሥራ በማገልገል የእግዚአብሔር ታማኝ አገልጋይ እንደነበር የራሱ መጽሐፍ ይመሰክራል::

ወጣቱ ሳሙኤል እግዚአብሔርን ለማገልገል በእግዚአብሔር ከተጠራ በኋላ በተሰጠው ሀብተ ክህነትና ሀብተ ምስፍና ወገኖቹ ዕብራውያንን ከባዕድ አምልኮት ነጻ በማውጣት አረማውያን ነገሥታትንም የገሠፀና ያንበረከከ ወደ እግዚአብሔር አምልኮ የመለሰ ለጥቅም የተሰለፉ መሪዎችንም ከመስዋዕት ይልቅ መታዘዝ ይበልጣል በማለት ከሥልጣናቸው ያሰወገደ ቀዳ.ሳሙ.ምዕ.15 ቁ.32-33 ለእውነተኛ መሪዎች ሥልጣን ከእግዚአብሔር ለምሳሌ የሳኦልን ሹመት ለዳዊት በማሰጠት ክህነትንና ነቢይነትን እንዲሁም ሥርዓተ መንግሥት አጣምሮ በመምራት የመረጠው እግዚብሔርን ያስደሰተ ታላቅ ነቢይና ካህን እንዲሁም ታማኝ የሕዝብ መሪ ነበር:: ሥራውንም ከሚከተሉት ጥቅሶች መገንዘብ ይችላል:: 1ኛ ሳሙ.ምዕ3ና21 ቁ.25ና27-28 ቀዳ.ሳሙ.ምዕ2 ቁ.22-25 ምዕ.3 ቁ11እና19 ምዕ.7 ቁ.8ምዕ.10 ቁ.1ምዕ.8 ቁ.4-9ምዕ.15 ቁ.22-23ምዕ.16 ቁ.11-13



ወዘተ ተመልከት::

2.2 <u>ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት ወልደ እሴይ</u>:-ረከብክዎ ለዳዊት ገብርዬ ብእሴ ምዕመነ ዘከመ ልብየ የሐ.ሥራ ም.13 ቁ.22 መዝ.88 ቁ.20 እንደሀስቤ የሚሄድ ታምኝ አገልጋዬ ዳዊትን አገኘሁት:: ቀዳ.ሳሙ.ምዕ13 ቁ.14 ተብሎ በቅዱስ እግዚአብሔር የተመረጠና የተነገረለት ቅዱስ ዳዊት ታላቅ የእግዚአብሔር ታማኝ አገልጋይና ከቅዱሳን አበው ነገረ ሥጋዌ በስፋትና በጥልቀት እግዚአብሔር ይቤለኒ ወልድየ አንተ ወአነ ዮም ወለድኩከ እግዚአብሔር አለኝ አንተልጄ ነህ እኔ ዛሬ ወለድኩህ ተብሎ መዝ.2 ቁ.7 ተካፈሉ አልባሰየ ወተአጸው ዲበ አራዝየ ልብሶቼን ለራሳቸው ተካፈሉ በቀሚሴም ላይ እጣ ተ ጣጣሉ ተብሎ መዝ.21 ቁ.16-18 እግዚአብሔር በመለከት ድምፅ ዐረገ ዘምሩ ለአምላካችን ዘምሩ ተብሎ መዝ.46 ቁ.5 መዝ.11 ቁ.5 መዝ.67 ቁ.1 ተብሎ የተነገለበት::

እግዚአብሔርና ሰው የሚወደው ለቤተክርስቲያንም ዛሬ የጸሎት መዝገብ ሆኖ እግዚአብሔር ሲመለክበት የሚኖረውን ጸሎት ለዓለምና ለቀጣዩ ትውልድ ያበረከተ ታላቅ የእግዚአብሔር ምርጥና የክርስቶስ ዘመነ ሥጋዌ በግልጽ ከጽንሰት እስከ እርገትና ዳግም ምፅዓቱ የተነገረበትና የተመሰከረበት መዝ.49 ቁ.3

ከኃያሉ አምላክ ከቅዱስ እግዚአብሔር:-

1. ሀብተ ክህነት
2. ሀብተ መንግሥት /ምስፍና/
3. ሀብተ መዊዕ
4. ሀብተ ትንቢት
5. ሀብተ ኃይል
6. ሀብተ በገና እና
7. ሀብተ ፈውስ 7ቱ ሀብታት የተሰጡት ቅዱስና ክቡር አባት ነው::

2..3 <u>ኤልያስ ቴስቢያዊ:-</u> ከክርስቶስ ልደት በፊት በ900 ዓ.ዓ የነበረ ኤልያስ በዘንበሪ ልጅ በአከአብ ጊዜ የእስራኤልን ሕዝብ

ከአምልኮ ጣዖት ነፃ ያወጣና አክአብንና ሚስቱ ኤልዛቤልን በእምነቱ ውጤት ያንበረከከ ታላቅ ነቢይ ነው:: ሥራዎቹም

1ኛ. የእስራኤል ህዝብና መሪዎቻቸው እግዚአብሔርን ማምለክ ትተው ጣዖት ስላመለኩ በዚህ ድርጊታቸው በእግዚአብሔር አምላክ በመቅናት ዝናብ ለዘርጠል ለመከር እንዳ ይዘንብ ሦስት አመት ከመንፈቅ ሰማይን የዘጋ ታላቅ ነቢይ ነበር:: ቀዳ.ነገ.ምዕ 17 ቁ.1-7 ያዕ.ምዕ.5 ቁ.17-18

2ኛ. በሲዶና ስራፕታ የነበረችውን መበለት ልጇ ቢሞትባት ከሞት ያስነሳና ቤቷን በበረከት የሞላ ቀዳ.ነገ.ምዕ.17 ቁ.17-24 እግዚአብሔር ኃይሉንና ፀጋውን የገለጠበት ነበር::

3ኛ. ይህ ነቢይ የእግዚአብሔር መምለኪያነ ጣዖት ነገሥታትንና ህዝቡን የቀጣበትና ወደ እራሱ አምልኮት የመለሰበት ኃይሉን የገለጠበት ሐቀኛ ነቢይ ነበር ቀዳ.ነገ.ምዕ.18 ቁ.21-40

4ኛ. የእግዚአብሔር ሰው ኤልያስ እግዚአብሔር በሰጠው ፀጋና ኃይል እግዚአብሔርን ስላስደሰተው በእምነቱና በሥራው ውጤት ለሰው ልጆች ሁሉ ዕድል ፈንታ የሆነውን መራራ ሞትን ሳይቀምስ በሕይወት ወደ ብሔረ ሕያዋን የገባ የእግዚአብሔር ምርጥ ነቢይ ነበር ነገ.ካል.ምዕ.2 ቁ.1-11 ተመልከት:: በመሆኑም በእግዚብሔር የተጠራና የተመረጠ ኤልያስ በእምነቱነና በሥራው እግዚአብሔር ስላከበረው ትውልድ ሁሉ ሲያወሳውና ሲያከብረው ይኖራል:: እግዚአብሔርን ስላስደሰተው በእምነቱና በሥራው ውጤት ለሰው ልጆች ሁሉ ዕድል ፈንታ የሆነውን መራራ ሞትን ሳይቀምስ በሕይወት ወደ ብሔረ ሕያዋን የገባ የእግዚአብሔር ምርጥ ነቢይ ነበር ነገ.ካል.ምዕ.2 ቁ.1-11 ተመልከት:: በመሆኑም በእግዚብሔር የተጠራና የተመረጠ ኤልያስ በእምነቱነና በሥራው እግዚአብሔር ስላከበረው ትውልድ ሁሉ ሲያወሳውና ሲያከብረው ይኖራል::

2.4 <u>ኢሳይያስ ወልደ አሞፅ</u>:- ነቢየ እግዚአብሔር ኢሳይያስ ከዓበይት ነቢያት አንዱ ሲሆን እግዚአብሔር አምላክ ሰው ሆኖ



ሰውን ለማዳን ያሰበውን የማዳን ሥራ ከጽንስ ጀምሮ እስከ ዕለተ ምፅዓት ድረስ ያለውን ነገረ ሥጋዌ በግልፅ የተናገረና የዓፈ ነቢይ ነው:: ይኸውም:-

1ኛ. ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች:: ኢሳ.ምዕ.7 ቁ.14 መዘቴ.ምዕ.1 ቁ.19-25 ኢሳ.ምዕ.9 ቁ.6-7

2ኛ. እነሆ በጽዮን የመሠረት ድንጋይን አስቀምጣለሁ የተፈተነውን የከበረውን የማዕዘን ደንጋይ የሚያምን አያፍርም ኢሳ.28 ቁ.16 የማዕዘን ድንጋይና መሠረት የተባለው ሰው የሆነው አምላክ ክርስቶስ ነው::

3ኛ. እነሆ ጌታ እግዚአብሔር እንደ ኃያል ይመጣል ክንዱም ስለእሱ ይገዛል ኢሳ.ምዕ.40 ቁ.3-5 እና ቁ.10-11 ክንድም የተባለው ሰውን ለማዳን ሰው የሆነው የአብ የባህርይ ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው::

4ኛ. ተመለከትሁ የሚረዳም አልተገኘም ስለዚህ የገዛ ክንዴ መድኃኒት አመጣልኝ:: ኢሳ.ምዕ.62 ቁ.5 ምዕ.65 ቁ.1

5ኛ. ጀርባዬን ለገራፊዎች ጉንጬንም ለጠጉር ነጪዎች ሰጠሁ ፊቴንም ከውርደትና ከትፋት አልመለስሁም:: ኢሳ.ምዕ.50 ቁ.6 ምዕ.53 ቁ.2-9

6ኛ. እነሆ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እፈጥራለሁ የቀደሙትም አይታሰቡም:: ኢሳ.ምዕ65 ቁ.17 በማለት ኀልፈተ ሰማይና ምድር የሚፈጸምና የማይቀር ቀጣይ የእግዚአብሔር የድኅነትና የዘለዓለም የህይወት መንግሥት ለቅዱሳን መላእክትና ለሰው ልጆች እንደሚፈቀድና እንደሚሰጥ በግልፅ የተናገረና የዓፈ ታላቅ ነቢይና የእግዚአብሔር ሰው መሆኑን በአጭሩ የተጠቀሱት መልእክቶች ያስገነዝባሉ::

2.5 <u>ኤርምያስ ወልደ ኬልቅያስ/ሕልቅያስ</u>/:- ነበየ እግዚአብሔር ኤርምያስ በይሁዳ ንጉሥ በኢዮስያስ ልጅ በኢዮአቄም ዘመን በ4929 ዓ.ዓ የነበረ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ629 ዓ.ዓ ማለት ነው:: ይህ ነቢይ እሥራኤላውያን በኃጢአታቸው በአረማውያን ንጉሥ በናቡከደነፆር በተማረኩበት ጊዜ በባዕድ ሀገር

እስራኤላውያንን ለመታደግ ከእግዚአብሔር ተመርጦ ለእግዚአብሔር ሥራ የተላከ ነቢይ ነው፡፡ በመሆኑም፡-

1. በሆድ ሳልሠራህ አውቄሃለሁ ከማሕፀንም ሳትወጣ ቀድሼ ሃለሁ ለአህዛብም ነቢይ አድርጌሃለሁ ብላቴና ነኝ እናገር ዘንድ አላውቅም አልችልም አትበል የማዝህን ሁሉ ትናገራለህ እኔ አድንህ ዘንድ ከአንተ ጋር ነኝና ከፊታቸው አትፍራ ቃሌን በአፍህ ውስጥ አኑሬአለሁ እንሆ ትነቅልና ታፈርስ ታጠፋና ትገለብጥ ትሠራና ትተክል ዘንድ በአህዛብና በነገሥታት ላይ ዛሬ አድርጌሃለሁ/ሾሜሃለሁ/ ተብሎ ኤር.ምዕ.1 ቁ.4-8 ቁ.10 ምርጫውን ከሙሉ ሥልጣንና ክብር ጋር የተቀበለ ነቢይ ነው፡፡
2. ጠቢብ በጥበቡ ኃያልም በኃይሉ ባለጠጋም በሀብቱ አይመካ ምህረትንና ፍርድን በምድር ላይ የማደርግ እኔ እግዚአብሔ ር መሆኔን በማወቁ በዚህ ይመካ እኔን ደስ የሚያሰኙኝ እነዚህ ናቸውና የሚለውን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ተቀብሎ በትክክል ያስተላለፈ ኤር.ምዕ.9 ቁ.23-24 በሰው የሚታመን ልቡም ከእግዚአብሔር የሚመለስ ሰው ርጉም ነው፡፡ ኤር.ምዕ.17 ቁ.5 እነሆ በፊታችሁ የሕይወትን መንገድና የሞትን መንገድ አድርጌአለሁ ኤር.ምዕ.21 ቁ.8 እኔ የቅርብ አምላክ እንጂ የሩቅ አምላክ አይደለሁም የሚለውን ኃይለ ቃል ያስተላለፈ
3. ልዑል እግዚአብሔር ለሥራው እንደ እርሱ መርጧቸውና ጠርቷቸው ለግል ጥቅማቸው ዘወር ያሉትን ነቢያት ሲገስፃቸው የእግዚአብሄርን ሥራ በቸልታ የሚሠራ /የሚያደርግ/ ርጉም ይሁን ያለ ኤር.ምዕ.48 ቁ.10
4. ያልጠፉነው ከእግዚአብሔር ምህረት የተነሣ ነው ርኅራኄው አያልቅምና ሰቆ.ኤር.ምዕ.3 ቁ.22 በማለት የእግዚአብሔርን ኃይልና ሥልጣን ፈቃዱንና ምህረቱን ለሰው ልጆች ያስተላለፈ ከእናቱ ማሕፀን ለሥራ በፈጣሪው የተመረጠና የተቀደሰ ታላቅ የእግዚአብሔር ነቢይና ምሥክር ነበር ስለታላቅነቱና ግዳጁን በትክክል የተወጣ ነቢይ ለመሆኑ



ሥራዎቹን የራሱ መጽሐፍ ይመሰክራል፡፡ ስለሆነም በእግዚአብሔር የተመረጠ ቅዱስና ክቡር እንደሆነ ትውልድ ሁሉ ሲያወሳውና ሥራውን ሲጠቀምበት ይኖራል፡፡

ከዚህ በላይ ዋና ዋና የሆኑትን የቀደምት አበውንና የታላላቅ ነቢያትን በእግዚአብሔር መመረጥና በባለሟልነታቸው የፈጸሙትን ሥራዎች በአጭሩ ለማሳየትና ለመግለጽ ተሞከረ እንጂ የእያንዳንዳቸው አበውና ነቢያት ምርጫና ሥራ ቢገለጥ በእግዚአብሔር ምርጫና ኃይል ከእነዚህ አበውና ነቢያት ያላነሰ የተቀደሰ ሥራ ተሠርቶ ለምሥክርነት በቅዱስ መጽሐፍ ተመዝግቦ እስከ ዓለም ፍፃሜ ድረስ የሰው ልጆችን ለድኅነትና ለሕይወት ሲጠራና ሲማርክ ይኖራል፡፡

ሐ. <u>ሐዋርያት</u>

ቅዱሳን ሐዋርያት እግዚአብሔር ወልድ ሰው ለሆነበት ለማዳን ሥራው ለሥራና ለክብር እስ ራሱ የመረጣቸው ቅዱሳን ናቸው እንዴት እንደመረጣቸውም በአጭሩ እንደሚከተለው እንመለከታለን፡፡

1ኛ በገሊላ ባህር ዓሣ አጥማጅ የነበሩትን የዮናን ልጆች ጴጥሮስንና እንድርያስን በኋላዬ ኑና ሰዎችን እንድታጠምዱ /ለድኅነት/ አጥማጆች እንድትሆኑ አደርጋችኋለሁ ማቴ.ምዕ4 ቁ.18

2ኛ በዚሁ ባህር በዓሣ ማጥመድ ይተዳደሩ የነበሩትን የዘብዴዎስን ልጆች . ያዕቆብንና ወንድሙ ዮሐንስን እነሱንም ዓሣ ሳይሆን ሰውን እንዲያጠምዱ /እንዲያስተምሩ/ ጠራቸው ማቴ.ምዕ.4 ቁ.21-22 ማር.ምዕ.1 ቁ.16-20 ዮሐ.ምዕ.1 ቁ.27-28

3ኛ. ቀጥሎም የሌዊን ልጅ ማቴዎስን ከአገር ውስጥ ገቢ ቀረጥ ስብሰባ/ከግብር/ መሰብሰብ ላይ እንዳለ አየና ተከተለኝ አለው ማቴ.ምዕ.9ቁ.9 ሉቃ.ምዕ.5 ቁ.27-28

4ኛ. በመቀጠልም የሐዋርያት ረዳቶች የሚሆኑ 72ቱ አርድዕትን ሁለት ሁለት እየሆኑ ከሐዋርያት ጋር ለአገልግሎት ለመላክ መርጦ ሾመ፡; ሉቃ.ምዕ.10 ቁ.1-12

እንዲሁም በዚሁ ምዕራፍ ቁጥር 16 ዮሐ.ምዕ13 ቁ.20

5ኛ. እንዲሁም ሌሎች ደቀ መዛሙርትና አይሁድ የህይወት ባለቤት ክርስቶስን ከመከተልና ከማገልገል ወደኋላ ሲያፈገፍጉ ሐዋርያት ግን እኛስ አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ እንደሆንህ አምነናል አውቀናልም ብለው ስለመለሱለት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ሲመልስ እኔ እናንተን አስራሁለታችሁን የመረጥኋችሁ አይደለምን? በማለት በእርሱ ለሕይወት አገልግሎት ሥራ መመ ረጣቸውን አረጋግጦጧል:: ዮሐ.ምዕ.6 ቁ.70

6ኛ. ቀጥሎም ከሐዋርያትና ከ72ቱ አርድዕት እንዲሁም ከ36ቱ ቅዱሳት አንስት ምርጫ በኋላ ለዚህ ሰውን ከኃጢአት ለማዳን ቅዱስ ዓላማ ቆራጥና አስተዋይ የነበረውን ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስን ይህ ሰው በአህዛብም በነገሥታትም በእስራኤልም ልጆች ፊት ስሜን ይሸከም ዘንድ ለእኔ የተመረጠ ዕቃ ነው በማለት መርጦና ሾሞ ልኮታል የሐ.ሥራ ምዕ.9 ቁ.15-16 ምዕ.13 ቁ.2-4 ቅዱስ እግዚአብሔር ቀደምት አበውንና ነቢያትን እንዲሁም ሐዋርያትንና ሌሎች ቅዱሳንን ለሥራ ሲመረጥና ከሙሉ ኃይልና ሥልጣን ጋር ነው ይህንም በሚከተለው አጫጭር ማስረጃ እንመለከታለን::

7ኛ. <u>ለቅዱሳን ከእግዚአብሔር የተሰጠ ኃይልና ሥልጣን</u>

1. <u>ለሙሴ:-</u> ረሰይከከ አምላኮ ለፈርዖን:- እኔ ለፈርዖን አምላክ አድርጌሃለሁ:: ዘጸ.ምዕ.7 ቁ.1 እግዚአብሔር ይህን ሲናገር ሙሴ ፈርዖንን ፈጥሮ ይመግበዋል ማለት አይደለም ቅዱሳንን አማልክት ዘበፀጋ ሲለሚላቸው ሙሴ ፈርዖንን በአምላክ ስልጣን የሚያንበረክከው መሆኑን ለመግለፅ ታስቦ ነው:: እንዲሁም በትሩን ወደ እባብ ውሃውን ወደ ደም በተ ሰጠው ፀጋና ሥልጣን ለውጦታል:: ዘጸ.ምዕ.7 ቁ.10-22 በመቀጠልም ሙሴ የኤርትራን ባህር ቀኝና ግራ በሰጠው ስልጣን በመክፈል እስራኤልን በየብስ አሻግሮ ጠላቶቻቸው ግብፃውንን አስጥሟል ዘጸ.ምዕ.14 ቁ.21-30 ከዚህም ሌላ እሥራኤላውያንን መና ከደመና በአምላኩ ፈቃዱ እያዘነበለት አርባ ዓመት መግቧል ዘጸ.ምዕ.16 ቁ.4-18 እንዲሁም የኤልያብ ልጆች ዳታንና አቤሮን በሙሴና በአሮን ላይ ስላመፁና እግዚአብሔርን ስላሳዘኑ መሬት ተከፍታ እንድትውጣቸው አድርጓል ዘጸ.ምዕ16 ቁ.29-35



2. <u>ኢያሱ ወልደ ነዌ:-</u> ከይሁዳ ነገድ የሆነ አካን ወልደ ከርሚ በእስራኤላውያንና በእግዚአብሔር ሕግ ያልተፈቀደውን የሰው ንብረት በመዝረፉና በመስረቁ ከነቤተሰቡና ንብረቱ ምድር እንድትወጠው አድርጓል ኢያሱ ምዕ.7 ቁ.25-26 እስርኤ ላውያን በእግዚአብሔር ኃይል የዮርዳኖስን ሙላት ግራና ቀኝ ከፍሎ በማቆም በየብስ እንዲሻገሩ በማድረግ ምድረ ርስት እንዲገቡ አድርጓል ኢያሱ ምዕ.3 ቁ.8-17

3. <u>ሳሙኤል ወልደ ሕልቃና:-</u> በእስራኤል ላይ የተሾመ ሳኦል ወልደ ቂስ ያልታዘዘውንና ሥልጣኑ ያልሆነውን መስዋዕት በመሰዋቱና የተከለከለውን የአረመኔ ንብረት በምርኮ ላይ ስለዘረፈነ ለእግዚአብሔር ስላልታዘዘ ከሥልጣኑ እንዲወገድ አድርጓል ቀዳ.ሳሙ.ምዕ.13 ቁ.8-14 እንዲሁም በሕዝበ እግዚአብሔር በእሥራኤላውያን ላይ ያመጸ አረመኔ የአማሌቅን ንጉሥ አጋግን ሳያል ተደልሎ ቢተወውም ሳሙኤል በሰይፍ ቆራርጦ ጥሎታል ቀዳ.ሳሙ.ምዕ.15 ቁ.32-33 ተመልከት::

4. <u>ኤልያስ</u>:- ኤልያስ ከእግዚአብሔር በተሰጠው ኃይልና ሥልጣን ትረዳው የነበረችው መበለት ልጅ ቢሞትባት ከሞት አስነስቶ አስረክቧታል ቀዳ.ነገ.ምዕ.17 ቁ.17-23 እንዲሁም የአካብንና የሚስቱ የኤልዛቤልን ካህናተ ጣዖት ለእግዚአብሔር ያቀረበውን መስዋዕት ከሰማይ እሳት ወርዶ ስለበላለት የእግዚአብሔርን አምላክነት ስላረጋገጠባቸው በሰይፍ አሳርዷቸዋል ቀዳ.ነገ.ምዕ18 ቁ.38-40 በእግዚአብሔ ር ኃይል ይህን ያደረገ ኤልያስ መራራ ሞትን ሳይቀምስ ከነሕይወቱ ወደ ብሔረ ህያዋን አርጓል:: ነገ.ካል.ምዕ.2 ቁ.8-11 ተመልከት::

5. <u>ኤልሳዕ</u>:-ይህ ሰው የኤልያስ ደቀ መዝሙር ነው በመሆኑም የኤልያስ ሀብተ መንፈስ ቅዱስ ስላደረበት ከነቢያት ወገን ባልዋ የሞተባት አንዲት ሴት ቤቷን በበረከት ከመሙላቱም በላይ ልጇ በድንገት ታሞ ቢሞትባት ወደ እግዚአብሔር ጸልዮ አስነስቶላታል ነገ.ካል.ምዕ.4 ቁ.32-37 እንዲሁም የሶርያ ንጉሥ ወልደ አዴር ሕዝበ እግዚአብሔር እስራኤልን ለማጥፋት በእልፍኝ የመከረውን ስላወቀና የቅዱሳን መላእክትም ረድኤት ስለተገለጸለት ለጥፋት የተላኩ የወልደ አዴር ሠራዊትን ዓይናቸውን በማሳወር ምግብ መግቦ ወደ ሀገራቸው የመለሰ ነቢይ ነው:: ነገ.ካል.ምዕ.6 ቁ.16-19 ይህ ነቢይ ከሞተም በኋላ አፅሙ አንድ ምውት አስነስቷል:: ነገ.ካል.ምዕ13 ቁ.20-21 ተመልከት::

6. <u>ኢሳይያስ ወልደ አሞፅ</u>:- ይህ ነቢይ እስራኤላውያን ጣዖት በማምለክ በእግዚአብሔር ላይ ስላመፁ በሚጠቀሙበት በሰማይና በምድር እንዲያዳኝባቸው ስልጣን የተሰጠው ነው:: ኢ.ሳ.ምዕ.1 ቁ.2 እንዲሁም ሂድ ይህን ሕዝብ መስማትን ትሰማላችሁ አታስተውሉም ማየትንም ታያላችሁ አትመለከቱም በማለት ጆሮአቸውን ድፈን ዓይናቸውንም አሳውር በማለት ከእግዚአብሔር የታዘዘ ነቢይ ነው::

7. <u>ኤርምያስ ወልደ ኬልቅዮስ</u>:- ይ ህ ነቢይ ገና ከእናቱ ማህፀን ለእግዚ.ብሔር ሥራ የተመረጠ ስለሆነ አትፍራ እኔ ከአንተ ጋር ነኝ እነሆ ትነቅልና ታፈርስ ዘንድ ታጠፋና ትገለብጥ ዘንድ ትሰራና ትተክል ዘንድ በአህዛብና በነገሥታት ላይ ዘሬ አድርጌሃለሁ/ሾሜሃለሁ/ የተባለ የእግዚአብሔር የኃይሉ መገለጫ ነቢይ ነው:: ኤ ር.ምዕ.1 ቁ.8-10 ኤር.ምዕ.42 ቁ.20-22 ተመልከት::

8. <u>ሕዝቅኤል ወልደ ቡዝ</u>:- ይህ ነቢይ እግዚአብሔርን የተ ከማምለክና ከመታዘዝ ወደ አመፁ እስራኤላውያን የተ ላከ ነቢይ ነው ይኸውም በእኔ ላይ ወደ አመፁ ወደ አመፀኞች የእስራኤል ልጆች እልክሃለሁ:: ሕዝ.ምዕ.3 ቁ.2-7



9 በማለት የተሾመና ግዳጁን የተወጣ ነቢይ ነው::

9. <u>ቅዱሳን ሐዋርያት</u>:- ሐዋርያት የሐዲስ ኪዳን የድኅነት የክርስቶስ ምርጦችና መልእክተኞች ናቸው:: የተሰጣቸውም ስልጣን ሄዳችሁ መንግስተ ሰማያት ቀርባለች ብላችሁ ስበኩ ድውዮችን ፈውሱ ሙታንን አስነሱ ለምፃሞችን አንፁ አጋንንትን አውጡ በከንቱ የተቀበላችሁትን በከንቱ ስጡ:: ማቴ.ምዕ.10 ቁ.8 እንዲሁም በማርቆስ ወንጌል ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሏቸዋል በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ በአዲስ ቋንቋም ይናገራሉ እባቦችን ይይዛሉ የሚገድልም ነገር ቢጠጡ አይጎዳቸውም እጃቸውን በድውዮች ላይ ይጭናሉ እነርሱም ይፈወሳሉ/ ይድናሉ/ ማር. ምዕ 16 ቁ.15-17 ለሐዋርያት ረዳቶች ለ72ቱ ደቀመዛሙርትም ሰብዓውም በደስታ ተመልሰው ጌታ ሆይ አጋንንት ስንኳን በስምህ ተ ገዝተውልናል አሉት አርሱም እንዲህ አላቸው ሰይጣን እንደ መብረቅ ከሰማይ ሲወድቅ አየሁ እንሆ እባቡንና ጊንጡን ትረግጡ ዘንድ በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ስልጣን ስጥቻችኋለሁ የሚጎዳችሁም ምንም የለም:: ሉቃ ምዕ.3 ቁ.17-19 እንዲሁም በሐዋርያት ሥራ ጴጥሮስና ዮሐንስ አርባ ዓመት የሆነውን ሽባ በክርስቶስ ስም ቆሞ እንዲሄድ አድርገውታል የሐ.ሥራ.ምዕ.3 ቁ.4-10 በመቀጠልም ጴጥሮስ በመንፈስ ቅዱስ ፊት የዋሹ ባልና ሚስት በክህደታቸው በአንድ ቀን በሞት እንዲቀጡ አድርጓል:: የሐ.ሥራ ምዕ.5 ቁ.5-11 እንዲሁም ምዕ.8 ቁ.7 ብዙ ድውዮችን ፈውሷል:: በመቀጠልም ይኸው ሐዋርያ ከ8 ዓመት ጀምሮ ሽባ የነበረውን ኤንያን ከመፈወሱም በላይ ዶርቃ ትባል የነበረችውን በጎ አድራጊ ከሞት አስነስቷል:: የሐ.ሥራ ምዕ.9 ቁ.33-41 ተ መልከት:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም በልስጥራን እግሩ የሰለለ ሽባ ቆሞ እንዲሄድ ከማድረጉም በላይ በልብሱ ጨርቅ ድውዮችን ይፈውስ ነበር::

የሐ.ሥራ ም.14 ቁ.8-10 ምዕ.19 ቁ.6-13 መመልከት ይቻላል:: ይህ ሁሉ ሊደረግ የቻለው በእምነታቸው ጥንካሬና እግዚአብሔር በስጣቸው ኃይልና ሥልጣን መሆኑን መገንዘብ ይቻላል::

ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ከሆነ የሚያጣው የለም የሚሳነውም የለም:: ዕለታዊ ፍጆታውንና ዕለታዊ ግዳጁን ለመፈፀም ከእግዚአብሔር ኃይልና ሥልጣን ተሰጥቶታልና ነው:: ሰው የሚቸግረው ከእግዚአብሔር አምልኮና ትዕዛዝ ሲለይ ብቻ ነው:: ምክንያቱም ወዘእንበሌየሰ ኢትክሉ ገቢረ ወኢምንትኒ ያለ እኔ ምንም ምን ማድረግ አትችሉም ዮሐ.ምዕ15 ቁ.5 ብሏልና:: ንበሩ ብየ ወአነሂ ብክሙ በእኔ ኑሩ እኔም በእናንተ እኖራለሁ:: ዮሐ.ምዕ.15 ቁ.4 ብሏልና ወእመሰ ነበርክሙ ብየይከውን ለክሙ በእኔ ብትኖሩ ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ የምትወዱትን ሁሉ ለምኑ ይሆንላችሁማል ብሏልና ነው:: ዮሐ.ምዕ.15 ቁ.7 ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ቅዱሳን አበው ነቢያትና ሐዋርያት ለማስረጃ ያህል ጥቂቶችን ጠቀስኩ እንጂ በእግዚአብሔር ፀጋ የተጠቀሙና ሰውና እግዚአብሔርን በተሰጣቸው ፀጋ ያገለገሉ ብዙዎች ናቸው ይልቁንም እኛ የማናውቃቸው እግዚአብሔር የሚያውቃቸው አገልጋዮቹ ብዙዎች ናቸው::

በመሆኑም ከዚህ በመቀጠል የእያንዳንዱን ሰማዕትና የእያንዳንዱን ፃድቅ ገድልና ትሩፋት ለአንባብያን ለማቅረብ የማቴሪያልና የጊዜ ችግር ስላለ አጠርና ጠቅለል ባለመልኩ ሁሉንም በሚያማክል ሁኔታ ለማቅረብ እንደሚከተለው ተመዝግቦ ይነበባል::

መ. <u>ቅዱሳን ሰማዕታት</u> እንደእምነታቸው ጽናትና እንደሥራቸው ጥራት በእግዚአብሔር ለክብርና ለሕይወት የተመረጡ ቅዱሳን ሰማዕታት:-

ቅዱሳን ሰማዕታት ተብለው በቤተክርስቲያን የሚጠሩት በአላውያን ነገሥታትና በአላውያን መሳፍንት ሥልጣን ፊት ቀርበው እግዚአብሔርን ካዱ ለጣዖት ስገዱ ለእኛ ሥጋዊ



ዓላማና ፓለቲካ ተገዙ ሲባሉ ፈጥሮ የሚመግበንን አምላክ እግዚአብሔርን አንክድም ለሰው ስራሽ ጣዖት አንሰግድም በማለት ሳይፈሩና ሳያፍሩ በእምነታቸው ለእግዚአብሔርና ለሰው የመሰከሩ የእምነት አርበኞች ናቸው:: ይህንም ሥራቸውን ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እስከሞት ድረስ ተደበደቡ ለሌሎችም መዘባበቻ ሆኑ በእስራትና በግርፋት ተፈተኑ በድንጋይ ተወግረው ሞቱ በማለት ሰማዕታት የተቀበሉትን ፀዋትወ መከራ በአጭሩ ገልፆታል:: ዕብ.ምዕ.11 ቁ.32-40

<u>የሰማዕታት መርህ/የሰማዕታት መመሪያ/</u>

ሰማዕታት ከሰው ወገን ሆነው ሰው ሆነው ተፈጥረው ለዚህ ሁሉ ፈተናና ጸዋተወ መከራ ሲበቁ እንዴት ቻሉ? ብለን ስንጠይቅ የዚህን ዓለም ከንቱነት የቀጣዩን ዓለም የእግዚአብሔርን መንግሥት ክብርና ሕይወት ወሳኝነት በእምነት ዓይን በማየት እንደሆነ እንረዳለን እንገነዘባለንም:: ለዚህም ሥራ ያበቃቸውንም የእግዚአብሔርን መመሪያ በአጭሩ እንደሚከተለው እንመለከታለን::

1ኛ. ብፁዓን አንትሙ ሶበ ይሰደዱክሙ ወይዘነጉጉክሙ ወይነቡኩሎ ዕኩየላዕሌክሙ እንዘ ይሄስው በእንቲአየ ሲነቅፉአችሁና ሊያሳድዱችሁ በእኔም ምክንያት ክፉውን ሁሉ በውሸት ቢናገሩባችሁ ብፁዓን ናችሁ በዚህም ደስ ይበላችሁ ዋጋችሁ በሰማያት ታላቅ ነውና:: ማቴ.ምዕ.5 ቁ.11-12 የሚለው::

2ኛ. ወኢትፍርሕዎሙ ለእለይቀትሉ ሥጋክሙ ወለነፍስክሙስ ኢይክሉ ቀቲሎታ ወባሕቱ ፍርሕዎ ለዘቦ ሥልጣን ወይክል ነፍሰ ወሥጋ ነቡረ አኅጉሎ በውስተ ገሃነም ሥጋንም የሚገሉትን ነፍስን ግን መግደል የማይቻላቸውን አትፍሩ ይልቅስ ነፍስንም ሥጋንም በገሃነም ሊያጠፋ የሚችለውን እግዚአብሔርን ፍሩ::ማቴ.ምዕ.10 ቁ.28

3ኛ. ኩሉ ዘየአምን ብየ በቅድመ ሰብእ አነሂ አአምኖ በቅድመ አቡየ ዘበሰማያት በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ ሁሉ እኔ

ደግሞ በሰማይ ባለው አባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ:: ማቴ.ምዕ.10 ቁ.32-33 ማር.ምዕ.8 ቁ.38 የሚለው::

4ኛ. ዘኢያጥብዐ ወዘኢነሥአ መስቀለ ሞቱ ወዘኢተለወ ድኅሬየ ኢይደሉ ሊተ ወኢይክል ይጸመደኒ. መስቀሉንም የማይዝ በኋላዬም የማይከተለኝ ለእኔ ሊሆን አይገባውም ሊያገለግለኝም አይችልም:: ማቴ.ምዕ.10 ቁ.38-39 የሚለው::

5ኛ. ወኩሉ ይጸልአክሙ በእንተ ስምየ ወይቀትሉክሙ ወኢትትሐጐል አሐቲ እምሥዕርተ ርእስክሙ ወበትዕግሥትክሙ ታጠርይዋ ለነፍስክሙ በሁሉም ስለስሜ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ ከራሳችሁም አንዲት ጠጉር ስንኳ አትጠፋም በመታገሳችሁም ነፍሳችሁን ታገኛላችሁ ነፍሳችሁን /ታድናላችሁ/ ሉቃ.ምዕ.21 ቁ.17-18· የሚለው::

6ኛ. እለ በተአምኖ ታጋደሉ ወሞዑ ነገሥተ ወአድምዑ ፍናዊሆሙ ተገበሩ ጽድቀ ወረከቡ ተስፋሆሙ እነሱ በእምነት መንግስታትን ድል ነሱ ጽድቅን አደረጉ የተሰጠውን ተስፋ አገኙ::ዕብ.ምዕ11 ቁ.32-40 የሚለውን ህያው አምላካዊ ቃል አብነት በማድረግ ሰማዕታት አንገታቸውን ለሰይፍ ደረታቸውን ለጦር ጠቅላላ ሰውነታቸውን ለእሳት በመስጠት የዚህን አለም መራራ ሕይወት በመንግስተ ሰማያት ጣዕመ ሕይወት ለውጠው ፈጣሪያቸው የተቀበለውን ፀዋትወ መከራ ከሞላ ጎደል የተቀበሉ የእግዚአብሔር ምሥክሮቹ ናቸው በዚህ ዓለምም ሆነ በመንግስተ ሰማያት የእግዚአብሔር የክብር ልጆች ናቸው::

ለምሳሌ ከላይ በተመዘገበው መሰረት የተጠቀሙ ጥቂቶቹ ቅዱስ ጊዮርጊስ፣ ቅዱስ ቂርቆስ፣ ቅዱስ ፋሲለደስ፣ ቅዱስ ፊቅጦር፣ ቅዱስ እስጢፋኖስ፣ ቅዱስ ገላውድዎስ፣ ቅዱስ መርምህናም ቅዱስ ሚናስ፣ ቅዱስ ቴዎድሮስ፣ ቅዱስ መርቆሪዎስ፣ የመሳሰሉት ናቸው::



መ. <u>ቅዱሳን ጻድቃን</u>፡- ቤተክርስቲያን ጻድቃን ብላ የምትጠራቸው ቅዱሳን ኩሉ ዘይገብራ ለጽድቅ ጻድቅ ውእቱ በከመ ዝግቱ ጻድቅ እርሱ ጻድቅ እንደሆነ ጽድቅን የሚያደርግ ሁሉ ጻድቅ ነው እንዳለው ቅዱስ ዮሐንስ 1ኛ ዮሐ.መል.3 ቁ.7 የህይወት ዘመናቸውን ከተድላ ዓለምና ከጣዕመ ዓለም ለይተው ፈቃደ ሥጋቸውን ለፈቃደ ነፍሳቸው አስገዝተው በፆም፣ በጸሎት፣ በስግደት፣ በምናኔ ጸንተው ዳዋ፣ ጥሰው ድንጋይ ተንተርሰው ቅጠል፣ ቀምሰው ጤዛ፣ ልሰው ድበፀ ዓራዊትን ግርማ ለሊቱን ታግሰው በዋሻ በፍርክታ በዱር በገደል በገዳም የሚኖሩ ሥጋ የለበሱ በኑሮዋቸው የመላእክት ወገኖች ናቸው::

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ጻድቃን ሲናገር ሁሉን እያጡ መከራን እየተቀበሉ እየተጨነቁ የበግና የፍየል ሌጦ ለብሰው ዞሩ ተንከራተቱ ዓለም አልተገባቸውምና በምድረ በዳና በተራራ በዋሻና በምድር ጉድጓድ ተቅበዘበዙ በማለት የመሰከረላቸው ናቸው:: ዕብ ምዕ 11 ቁ.37-38 ወ.ዘ.ተ

## 2. <u>የጻድቃን መርህ /የጻድቃን መመሪያ/</u>

1. ባአ፡ እንተ፡ ጸባብ፡ አንቀጽ ወድዕቅት ፍኖት እንተ ትውስድ ውስተ ሕይወት ዘለዓለም፡- በጠበበው ደጅ ግቡ ወደ ጥፋት የሚወስደው ደጅ ሰፊ ነውና ወደ ሕይወት የሚወሰደው ደጅ ግን የጠበበ መንገዱም የቀጠነ ነውና የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸው:: ማቴ ምዕ 7 ቁ.13-14 የሚለውን፡-
2. ዘያፈቅር አባሁ ወእሞ እምኔየ ኢይደሉ ሊተ ወኢይከል ይጸመደኒ ከእኔ ይልቅ አባቱን ወይም እናቱን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባውም ሊያገለግለኝም አይችልም ማቴ ምዕ 10 ቁ.37-38 ያለውን፡-
3. ወዘይፈቅድ ያድኅና ለንፍሱ ለይግድፋ ወዘሰ ገደፋ ለነፍሱ በእንቲአየ ይረክባ ወምንተ ይበቁዖ ለሰብእ ለእመ ኩሎ ዓለመ ረብሃ ወነፍሶ ኀጉለ ነፍሱን ሊያድን የሚወድ ሁሉ ያጠፋታል ስለኔ ግን ነፍሱን የሚያጠፋ ሁሉ ያገኛታል /

/ያድናታል/ ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ/ገንዘቡ ቢያደርግ/ ነፍሱንም ቢያጎድል/ቢበድል/ ምን ይጠቅመዋል ወ.ዘ.ተ. ማቴ 16 ቁ.25-30 የሚለውን

4. አሌ ለክሙ እለትጸግቡ ይእዜ እስመ ትርኀቡ አሌ ለክሙ እለ ትስሀቁ ይእዜ እስመ ትበክዩ ወትላህው እናንተ አሁን የጠገባችሁ ወዮላችሁ ትራባላችሁና እናንተ አሁን የምትስቁ ወዮላችሁ ታዝናላችሁና ታለቅሱማላችሁና ሉቃ 6 ቁ.25 ወ.ዘ.ተ የሚለውን:-

5. ዑቁ ርእስክሙ ኢታክብዱ ልበክሙ በበሊዕ ወበስታይ ወበሐልዮ መንበርት ወትብጽሐክሙ ይእቲ ዕለት ግብተ ትግሁ እንከ በኩሉ ጊዜ ከመ ትክሀሉ አምስጠ በጸሎትክሙ እም ኩሉ ዘይመጽእ ነገር ግን ልባችሁ በመጠጥ ብዛትና በስካር ለትዳርም በማሰብ እንዳይከብድ ያቀንም በድንገት እንዳይመጣባችሁ ለራሳችሁ ተጠንቀቁ ሉቃ 21 ቁ.34-35 ወ.ዘ.ተ የሚለውን

6. ኢታፍቅርዎ ለዓለም ወኢዘሀሎ ውስተ ዓለም ወዘሰ አፍቀሮ ለዓለም ኢሀሎ ፍቅረ እግዚአብሔር ላዕሌሁ እስመ ኩሉ ዘሀሎ ውስተ ዓለም ፍትወቱ ለሥጋ ወፍትወቱ ለዓይን ወሰራሁ ለመንበርት ኢኮነ ዝንቱ እምኀበ አብ አላ እምዓለም ውእቱ ዓለሙኒ የኃልፍ ወፍትወቱኒ የኃልፍ ዘሰ ይገብር ፈቃደ ለእግዚአብሔር ይነብር ለአለም 1ኛ ዮሐ መል ምዕ 2 ቁ.15-17 ያዕ ምዕ 4 ቁ.4 አለምን ወይም በአለም ያሉትን አትወደዱ በአለም ያለው ሁሉ እርሱም የስጋ ምኞትና የአይን አምሮት ስለገንዘብም መመካት ከአለም ስለሆነ ከአባት ከእግዚአብሔር ስላልሆነ ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት የእግዚአብሔር ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም ዓለሙም ምኞቱም ያልፋል የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ግን ለዘላለም ይኖራል ወ.ዘ.ተ የሚለውን ሕያው አምላካዊ ቃል አብነት በማድረግ ጠቅላላ ሕይወታቸውን ለገድል ለትሩፋት በመስጠት የዚህን ዓለም መራራ ሕይወት በመንግስተ ሰማያት ጣዕመ



ሕይወት ለውጠው ፈጣሪያቸውን በስራቸው መስለው ሕይወታቸውን በጽድቅ መንገድ የመሩ የአማንያን አብነትና የእግዚአብሔር የክብር ልጆች ናቸው ጻድቃን የሚባሉት እነማን እንደሆኑ ለምሳሌ ጥቂቶቹን ብንጠቅስ አቡነ ዜና ማርቆስ፣ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ፣ አቡነ ተ ክለ ሃይማኖት ቅዱስ፣ ያሬድ ተሰዓቱ ቅዱሳን አቡነ ኢየሱስ ሞዓ አቡነ ሳሙኤል ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉት ናቸው::

# ምዕራፍ 5

## የቅዱሳን አማላጅነት

ከሁሉ በፊት ምልጃ ማለት ምን ማለት ነው? የቃሉን ትርጉም ማወቅ ተገቢ ነው ምልጃና ማስታረቅ ተመሳሳይና የይቅርታ ሥራ ጠባዮች ናቸው ማስታረቅም ሆነ ምልጃ የሚፈጸመው በሦስት ወገን ነው::

ሁለት አካላት /አባላት/ ሲጋጩ ሦስተኛ አካል /አባል/ ችግሩን ለመፍታት ጣልቃ ገብቶ ይማልዳል ያስታርቃል የማማለድና የማስታረቅ ትርጉም በአጭሩ ይህን ይመስላል::

ይሁን እንጂ እኔ በዚህ ጽሁፍ ለአንባቢያን ላስገነዝብ የምፈልገው በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የተፈጸመውንና በመፈጸም ላይ ያለውን የምልጃና የማስታረቅ ባህሪያትን ይመለከታል::

በመሰረቱ መማለድና መታረቅ የኃያሉ እግዚአብሔር ባህርይና ፈቃድ ሲሆን ማማለድና ማስታረቅ ግን ለሰው ከእግዚአብሔር የተሰጡ የጸጋ ሀብቶች ናቸው:: እነዚህም ሁለት አይነት ናቸው እነርሱም:- 1ኛ. የእግዚአብሔርን ሕግ በመጣስ የበደለ ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር ማስታረቅ 2ኛ. ሰውን ከሰው ጋር ማስታረቅ ናቸው ይኸውም የበደለ ሰውን ካልበደለው ሰው ጋር ማስታረቅ ማለት ነው ይህም ብፁዓን መሐሪያን ያለውን ይመለከታል ማቴ.ምዕ 5 ቁ.9

እግዚአብሔር ከምንም ከማንም ጋር አይጋጭም አይጣላም ህይ ዓይነቱ ባህርይም በእርሱ ዘንድ የለም

የእግዚአብሔር ባህርይ ምህረት ርኅራሄና ቸርነት ፈጥሮ ሕይወትን መስጠትና መመገብ ብቻ ነው። ስለሆነም እግዚአብሔር የማማለድና የማስታረቅ ሥራዎችን በሰው ሥራ ዎች ገብቶ አይሰራም የእርሱ ሥራ መማለድና መታረቅ ብቻ ነው።

በእርግጥ እግዚአብሔር ለሰው እንዲጠብቀው የሰጠው ህጉ ሲጣስ አምልኮቱ/መመለኩ/ ሲካድ መግቦቱ ሲዘነጋ ሰዎች ህጉን እንዲጠብቁና በአምልኮቱ ወደ እርሱ እንዲመለሱ በአባትነቱ ይቀጣል ይህ ግጭት አይደለም ተግሳጽና ትምህርት ነው የማማለድና የማስታረቅ ባህሪይና አቅም/ሥራ/ምን እንደሆነ ምን ያህል እንደሆነ ሰዎች ልናውቅ ይገባናል።

መማለድና መታረቅ የሰዎች ባህርይ እንጂ የእግዚአብሔር ባህርይ አይደለም ከላይ እንደተጠቀሰው የእግዚአብሔር ባህርይ መማለድና መታረቅ ነው ከዚህ ወጥቶ እግዚአብሔር ያማልዳል እግዚአብሔር ያስታረቃል ማለት ፍፁም ስህተት ነው የማንዛቤ ማነስም ነው እግዚአብሔር ስል ክርስቶስ ማለቴ ነው።

ከዚህ በመነሳት በአሁኑ ጊዜ በተለያየ አመለካከት ስም በመሰየም የሃይማኖት ሥርዓትን የሚያራምዱ ድርጅቶችና በውስጡ የሚገኙ ሰዎች የመማለድንና የማስታረቅን ባህርይ ያወቁትና የተገነዘቡት አይመስሉም ምክንያቱም ሰውን ለማዳን ሰው የሆነውን አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስን አማላጅና አስታራቂ ነው ብለው በመፈረጅ ሲናገሩና ሲዘምሩ ይሰማሉ።

ተሳስተዋል፤ ከማንው የሚያስታርቀው? ከማነው የሚማልደው? እርሱ ማን ሆኖ በሰብእና ብቻ ከተፈረጀ ደኅነት አልተፈፀመም ማለት ነው በዕለተ አርብ ባፈሰሰው ደሙ አድኖናል የሚሉ ከሆነ ፍፁም አምላክ ፍፁም ሰው መሆኑን መቀበል ግድ ይሆናል ከዚህ ወጥቶ ግን ያማልዳል ያስታርቃል ማለት ከባህሪይ አባቱ ከአብ ከባህርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስና ከራሱ ወጭ የሆነ ሌላ አምላክ እንዳለ አድርጎ ማሳየት ይሆናል ስለሆነም ከስህተታቸው ሊታረሙና ሊገነዘቡት



ይገባል። የእግዚአብሔር አብንና የእግዚአብሔር ወልድን የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስንም የባህርይ አምላክ መሆንና የሥልጣን፣ የባህርይ፣ የፈቃድ፣ አንድነታቸውን፣ ማወቅና በአንድ ልብ የሚያውቁ በአንድ ቃል የሚናገሩ በአንድ ሕይወት የሚኖሩ ሦስት አካላት መሆናቸውን መገንዘብ ተገቢ ነው።

ይሁን እንጂ እነዚህ በክርስቶስ ላይ የተሳሳተ አመለካከት ያላቸው የስህተት አራማጆች ክርስቶስ በመዋዕለ ሥጋዌው/ በዘመነ ስጋዌው/ ለታከታዮቹ ደቀመዛሙርት ለማስተማር የተ ጠቀማቸውን መልዕክቶችና ቃላት በራሳቸው አመለካከትና ትርጉም በመጠቀም ባልገባቸው ነገር ከስህተት የወደቁ ይመስላል ምክንያቱም ክርስቶስ በሐዲስ ኪዳን ትምህርቱ ሲጠመቅ፣ ሲጾም፣ ሲፀልይ፣ ሲሰግድ ሲማጸን፣ ወ.ዘ.ተ ይነበባል ይታያል ይህ አይነቱ ስራ ትምህርት ነው። ከዚህ ያለፈ ትርጉም የለውም መጠመቁ ሰው በጥምቀት ከስላሴ ተ ወልዶ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሚሆን ለማስተማር ነው። ሐዮ.ምዕ 3 ቁ.3 እና 5 ማቴ.ምዕ 28 ቁ.19-20 ወ.ዘ.ተ መጾሙ ሰው በጾም ዲያቢሎስን ድል እንዲያደርግ ለማስተማር ነው ማቴ ምዕ 4 ቁ.1-5 ምዕ 6 ቁ 16 ምዕ 17 ቁ.21 ወ.ዘ.ተ መጸለዩ ጸሎት የማምለክና የመገዛት ምልክት ከመሆኑም በላይ የኃይል መሣሪያ እንደሆነ ለማሳየት ነው። ማቴ ምዕ 26 ቁ.41 ወደፈተና እንዳትገቡ ተግታችሁ ጸልዩ እንዳለ ወ.ዘ.ተ መስገዱ ከእርሱ ሌላ አምላክ ኖሮ አይደለም ሰዎች ለፈጣሪያቸው መስገድ እንዳለባቸው ለማስተማር እንደሆነ ያስረዳል መማጸኑ ሰዎች ከአቅማቸው በላይ የሆነ ፈተና ሲደርስባቸው ለማስተ ማር እንጂ እርሱ ይህ ሁሉ የሚያስፈልገው ሆኖ አይደለም። የሚያስፈልገው ቢሆንማ አባት ሆይ የምለምንህ እዚህ ስለቆሙት እንጂ ስለ እኔ አይደለም ባላለም ነበር ዮሐ ምዕ.11 ቁ42 ወ.ዘ.ተ እንግዲህ እነዚህን ከላይ የተጠቀሱትን የክርስትና ሥነ ምግባሮች በተግባር ስላሳየና ስላስተማረ እንደ ፍጡር በመቁጠር ያማልዳል በማለት እራሳቸው ባልገባቸው ነገር

ተሳስተው ሰውን ሁሉ በስላ የፅርፈት አንደበታቸው ሲያሳስቱ ይታያሉ::

ሌላው ከስህተት ላይ የጣላቸው አመለካከታቸው የክርስቶስን የባህርይ አምላክነት አለማወቅና ሐዋርያት በዘመነ ስብከታቸው የተናገሩዋቸውን ቃላት ትርጉማቸውን አለመገንዘባቸው ነው:: ለምሳሌ በቅዱስ ወንጌል 1ኛ ሰበስ ታፈቅሩኒ እምተፈሳሕክሙ በሐዊሮትየ ኀበ አብ እስመ ውእቱ አብ የዐብየኒ ብትወዱኝስ ወደ አብ በመሄዴ ደስ ባላችሁ ነበር::

አብ ከእኔ ይበልጣልና የሚለውን አነጋገር አለመገንዘብ፣ ይህ ማለት አብ ያከብረኛል ወደ አብ በመሄዴ ደስ ሊላችሁ ይገባል ሲል እንደ አብ እሱም አምላክ መሆኑን ለመግለፅ እንደሆነ፣ ይበልጠኛል ቢልም ወልድ በተለየ አካሉና በከዊነ ቃል ባህርይ የሰው ስጋን የተዋሐደውና በለበሰው ሥጋ መከራን መስቀልን የሚቀበል መሆኑን ለመግለጽ እንደሆነ አብ በተለየ አካሉና በከዊነ ልብ ባህርይ ሥጋን መከራ መስቀልን ሲቀበልበት ያልተ ዋሀደው መሆኑን ለማስገንዘብ እንደሆነ ማወቅ ይገባል:: ዮሐ ምዕ 14 ቁ.28 ዕብ ምዕ 2 ቁ.9 ወ.ዘ.ተ

2ኛ. ወይቤላ እግዚእ ኢየሱስ ለማርያም መግደለዊት ኢትልከፍኒ እስመ ዓዲ ኢዐረገ ኀበ አቡዬ ወሑሪ ባህቱ ኃበአኀውየ ወበሊዮሙ

አዐርግ ኃበ አቡየ ወአቡክሙ ኀበ አምላኪየ ወአምላክክሙ ገና ወደ አባቴ አላረግሁምና አትንኪኝ ነገር ግን ወደ ወንድሞቼ ሂደሽ እኔ ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ ዐርጋለሁ በያቸው ያለውን ይህ ማለት አቡየ ያለው ከአብ መወለዱን እንዲሁም አቡየ ያለው የእርሱ የባህርይ አባት መሆኑን አቡክሙ ያለው የእኛ የጸጋ አባት መሆኑን ለመግለፅ እንደሆነ አምላኪየ ያለው እርሱ ራሱ የተዋሀደውን ሥጋ ፈጥሮታልና ነው አምላክክሙ ያለው በጥንተ ተፈጥሮ በጥምቀት በሐዲስ ተፈጥሮ እኛን ፈጥሮናልና ስለሆነም የፈጠ ረውን ሥጋ በተለየ አካሉ በከዊነ ቃል ባህርይ ስለተዋሐደው ፈጥሮ መዋሀዱን ለመግለፅ አስበ ኀበ አምላኪየ አለ በአብና



በወልድ መካከል ወልድ ሰው ስለሆነ ልዩነት የለም በዕሪና አንድ ናቸው እርሱ እራሱ እግዚአብሔር ወልድ እኔና አብ አንድ ነን ሲል መስክሮአል:: ዮሐ ምዕ 20 ቁ.17 ምዕ 10 ቁ.30 ከዚህ ውጭ የክርስቶስን ትምህርት አጣሞ መተርጎም አደጋ ስለሚያስከትል መጠንቀቅ ያስፈልጋል::

3ኛ. ቅዱስ ጳውሎስ ለሮም ክርስቲያኖች በጻፈው መልዕክቱ ሮሜ ምዕ 8 ቁ.33 እና 34 ላይ ወመኑ ውእቱ እንከ ዘይትዋቀሶሙ ለኅሩያነ እግዚአብሔር ለእመ ለሊሁ ያጸድቅ ወመኑ ዘይኴንን ክርስቶስ ሞተ ወተንሥአ እሙታን ወሀሎ ይነብር በየማነ እግዚአብሔር ወይትዋቀስ በእንቲአነ እግዚአብሔር የመረጣቸውን ማን ይከሳቸውል? የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው የሚኮንንስ ማን ነው? የሞተው ይልቁንም ከሙታን የተነሳው በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው ደግሞ ስለእኛ የሚማልደው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው:: ተብሎ በቅዱስ መጸሐፍ ተፅፏል ሐዋርያው ይህን ሲናገርና ሲጽፍ በክርስትናና በሰው ልጆች ደኅነት በእግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ፍፁም አምላክነትና የማዳን ሀይል ተመክቶ የተናገረውና የጻፈው መልክት ነው::

ታዲያ የሐዋርያው መልዕክት ያልገባቸው ሰዎች ይትዋቀስ የሚለውን የግእዝ ቃል ይማልድልናል ብለው ተ ርጉመውታል ተሳስተዋል ይትዋቀስ ማለት ትርጉሙ ይመስክራል ይፈርዳል ያስገነዝባል ይገልፃል ማለት እንጂ ይማልዳል ማለት አይደለም ሐዋርያው በድህንነታችን ተመክቶ ሲናገር ክርስቶስ አድኖናል እኛም ድነናል እንግዲህ እግዚአብሐ ር በመረጣቸው እግዚአብሔር ለደኅንነት በሾማቸው ላይ የሚፈርድ ማን ነው? እኛን ያዳነን ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ በአብ ቀኝ /ዕሪና/ ተቀምጧል ብንበድል ዳኛው እርሱ ነው ለመዳናችንም ምስክሩ ያዳነን እርሱ ነው ፍርዱም እውነት ነው በማለት ምስክርነቱን ጽፏል ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስም በወንጌሉ በምዕ 5 ቁ.22-23 ፍርዱን ሁሉ ለወልድ ሰጠው እንጂ አብ በአንድ ሰው እንኳን አይፍርድም ያለውን በትክክል

በግልጽ ለመተርጎምና ለማስቀምጥ የሄደበት መንገድ መሆኑን መገንዘብ ይገባል::

ሐዋርያው የሄደበት ትርጉም ይህ ከሆነ ያማልደናል ለምን ይሉታል? በአብ ቀኝ ተቀምጧል ነው እኮ የሚለው ሐዋርያው ከባሕርይ አባቱ ከአብ ከባህርይ ህይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በዕሪና በመንበረ ዙፋኑ ከተቀመጠ በኋላ ምልጃ አለ እንዴ? ተቀምጠማ ምልጃ የለም ማንን ከማን ነው የሚያማልደው እርሱ እኮ አምላክ ነው ይኸው ሐዋርያ አባቶች ለእነሱ ናቸውና ከእነርሱም ክርስቶስ በሥጋ መጣ እርሱም ከሁሉ በላይ ሆኖ ለዘላለም የተባረከ አምላክ ነው ብሎ ምሥክርነቱን ገልጾአል እንዲህ ከሆነ ክርስቶስ ምልጃ የሚቀበል ታራቂና ይቅር ባይ እንጂ ዛሬ እርሱ አማላጅ አይደለም ሮሜ ምዕ 9 ቁ.5 እርሱ ራሱ የማማለድና የማስታረቅን ሥራን ለሐዋርያትና ለተከታዮቹ ለካህናት በአጠቃላይ ለቤተክርስቲያን እንዲህ በማለት አስረክቧል::

አንሰ ሰባህኩከ በዲበ ምድር ፈጺምየ ግብረ ዘወሀከኒ ከመ እግበር እኔ ላደርገው የሰጠኸኝን ሥራ ፈጽሜ በምድር አከበርኩህ በማለት የመማለድና የማስታረቅን ሥራ በባህርይ አባቱ በአብ በባህርይ ህይወቱ በመንፈስ ቅዱስ ፊት ለሐዋርያትና እስከ ዓለም ፍጻሜ ለሚነሱ ካህናትና ለቤተ ክርስቲያን አስረክቧል ትምህርቱና ቁም ነገሩ ይህ ከሆነ ከእውነት የራቃችሁ አስመሳይ አማኞች ስህተቶቻችሁን አርሙ ክርስቶስ ተማላጅና ታራቂ እንጂ አማላጅ አይደለም የማማለድ ሥራን ለቅዱሳንና ለቤተክርስቲያን ሰጥቶአል ዮሐ ምዕ 17 ቁ.4 ተመልከት ወ.ዘ.ተ

4ኛ. ደቂቅየ ዘንተ እጽህፍ ለክሙ ከመ ኢታአብሱ ወእመኒ በዘአበሰ ጰራቅሊጦስ ብነ ኀበ አብ ኢየሱስ ክርስቶስ ልጆቼ እንዳትበዱሉ ይህን እጽፍላችኃለሁ ከእናንተ የበደለ ቢኖር ከአባታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ የተሰጠን ጰራቅሊጦስ መንፈስ ቅዱስ ይቆጣጠረናል ይላል የግዕዙ መልዕክት የአማርኛው መልዕክት ደግሞ ማንም ኃጢያት ቢያደረግ



ከአብ ዘንድ ጠበቃ አለን እርሱም ጻድቅ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: ይላል የአማርኛው መልዕክት ግን ጭብጡን ለቆ ተተርጉሟል ምክንያቱም ጰራቅሊጦስ ኢየሱስ አይደለም ኢየሱስም መንፈስ ቅዱስ አይደለም ከአብ ዘንድ የሚለውም አብ ያለው እግዚአብሔር አብ አይደለም አብ የተባለው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ትርጉሙም አባት ማለት ነው የአብንም ስም ወሰደ ማለት አይደለም ይኸውም ከጎኑ በፈሰሰ ማየገቦ ተጠምቀን በጥምቀት ከስላሴ ስለወለደን ነው:: መንፈስ ቅዱስም ኃጢአት እንዳንሰራ የሚቆጣጠረን በተጠመቅን ጊዜ ስላደረገብ ማደሪያው ስለሆንን ነው:: ከዚህ ትርጉም ወጥሮ ክርስቶስን ጠበቃችን ማለት ድፍረትና ስህተት ነው:: 1ኛ ዮሐ መል ምዕ 2ቁ.1-2 የመልእክቱ ሀሳብ እንደ አማርኛው ትርጉም ቢሆን ኖሮ መልእክቱን የጻፈ ወንጌላዊ ዮሐንስ በዚህ መልዕክት ምዕ 5 ቁ.20 ላይ የእግዚአብሔር ልጅ እንደመጣ እናውቃለን እውነትም በሆነው በእርሱ አለን እርሱም ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: እርሱ እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት ነው ብሎ አይጽፍም ነበር ሐቁ ይህ ነው አንሳሳት

5ኛ. ሌላው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የኦሪት ሥርዓት ያለፈና የወንጌል ወይም የሀዲስ ኪዳን ሥርዓት የጸና እንደሆነ ለዕብራውያን ሲገልጽ የጻፈውን መተርጎም የተሳናቸው ሰዎች ብዙ ሲሉ ይሰማል ይኸውም ወደ ዕብራውያን ሰዎች ምዕ 7 ቁ.25 ላይ የተመዘገበው ቃል ነው ይህ ቃል በግእዙ «ወይክል አድኅኖቶሙ ለዝሉፉ ለእለ ይቀርቡ ሃበ እግዚአብሔር አንተ መንገሌሁ እስመ ለግሙራ ሕያው ውእቱ ወይተነበል ሎሙ ይላል» ትርጉሙም ወደ እግዚአብሔር ለሚቀርቡ ሁሉ ማዳን ይችላል ፈፅሞ ለዘላለም ሕያው ነውና ይለምንላቸዋልም ይላል ይለምንላቸዋል የሚለው ምንድን ነው የሚለምንላቸው? እርሱ ተለማኝ እንጂ ለማኝ አይደለምና ትክክለኛ ትርጉሙ ግን ይለመናቸዋል ይታረቃቸዋል ማለቱ ነው ይለምንላቸዋል የሚለው ምንድንነው የሚለመነው አማርኛው መልዕክት ደግሞ የማይለወጥ ክህነት አለው ስለእነርሱም ሊያማልድ ዘወትር

በህይወት ይኖራል ስለዚህም ደግሞ በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል? በዚህ መሰረት በአማርኛ መልዕክት የተሰጠው ትርጉም የሐዋርያውን ሃሳብና መንገድ የለቀቀ ነው ማለት ይቻላል ኢየሱስ ክርስቶስ ክህነትን ለማዳን ሥራ ለካህናት የሰጠ አምላክ እንጂ ፍጡር ሆኖ ክህነትን ከማንም አልተቀበለም በማይለወጥ ክህነት ሊያማልድ ዘወትር ይኖራል:: ያለውም አባባል ኢየሱስ ክርስቶስ በለበሰው ሥጋ ለማማለድ ሲል በመሬት አይኖርም በተዋሃደው ሥጋ የማዳን ሥራውን ፈጽሞ የማማለድ ሥራን ለሐዋርያትና ለተ ከታዮቻቸው ካህናት አስርክቦ ወደ መንበረ ክብሩ ተመልሶ አርጓል እውነቱ ይህ ነው::

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የሄደበት ሃሳብና መንገድ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለድህነት በሰራው የጥምቀት ሥርዓትና በስሙ እንዲሁም ለጥሙቃን በሰጠው በስጋውና በደሙ መስዋዕትነት ሰውን ሲዋሃደውና ሲታረቀው/ሲታረቅበት/ ይኖራል ማለት እንደሆነ የሀዋርያው ሃሳብና ትርጉም ይህ ነው ከዚህ ውጭ ክርስቶስን አማላጅ ማድረግና ወደ ፍጡር ማውረድና መጎተትን ስለሚያስከትል ልንጠነቀቅ ይገባል ወዘተ

እንግዲህ የማማለድና የመማለድ ሥራዎች ከማን ላይ እንደተቀመጡ ከላይ በተሰጡት ማስረጃዎች ከተመለከትን የማማለድ ሥራን ምልጃን የመቀበል ሥራ የማን እንደሆነ በሚከተሉት ማስረጃዎች እንመለከታለን:-

## ምዕራፍ 6.

## <u>የቅዱሳን ምልጃ በብሉይ ኪዳን</u>

ምልጃ ወይንም ማስታረቅ ከላይ በመቅድሙ እንደተ ጠቀሰው በሁለት ወገኖች በበዳይና በተበዳይ መካከል በሦስተኛው ወገን የሚፈጸም የሰላም መንገድ ነው ይህ ጉዳይ በሰውና በሰው መካከል የሚፈጸም ሲሆን አሁን በያዝነው ሥነ-ጽሑፍ ግን በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የሚፈፀም ምልጃና እርቅ ነው::

ይህም ከእግዚአብሔር ለሰው የተፈቀደና የተሰጠ የጸጋ ሀብት



ነው ይህ የምልጃና የዕርቅ መንገድ ለሰው ከእግዚአብሔር ሳይፈቀድ ቢቀር ኖሮ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያለው የሰላምና የህይወት ጉዞ ጭንቀትና ውጥረት የተሞላ ሆኖ ይቅር ነበር ማለት ይቻላል ይህ እንዳይሆን ነው ቅዱስ እግዚአብሔር በርሱና በሰው መካከል ሰላምና የተረጋጋ ህይወት እንዲኖር የምልጃና የእርቅ እንዲሁም የሰላምን መንገድ የከፈተው ይህንንም የምልጃና የእርቅ ጉዳይ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል እንዴት እንደሚፈጸምና እንደተፈጸመ በብሉይ ኪዳን የነበሩ የቅዱሳን ሰዎችን የምልጃና የእርቅ አፈጻጸም በሚከተሉት ተጨባጭ ማስረጃዎች መገንዘብ ይቻላል::

1. <u>አብርሃም አበ ብዙሃን</u>:- እግዚአብሔር በሰዶምና በገሞራ ሰዎች አመጽና ኃጢአት ስላዘነ ለሌላው ወገን የጥፋት አብነት እንዳይሆኑ ለማጥፋት /ለመቅጣት/ አስቦ ቀሳፍያን ሰብአ መላዕክት ስለላከ ጻድቁ አብርሃም በዚያች አገር ከተማ 50 ጻድቃን ቢገኙ አትምርምን? በማለት ጥያቄ አቅርቦ እግዚአብሔርም ይቅርታ ለማድረግ ለአብርሃም ገልጾለት ሳለ እንኳን ሃምሳ ጻድቃን 10 እንኳን ጻድቃን ባለመገኘታቸው ውሳኔው ተግባራዊ ሊሆን ችሏል:: ምልጃወቅ ግን ተቀባይነት አግኝቶ እንደነበር ታሪኩ በትክክል ያሳያል ኦሪ ዘፍ 18:22-23
2. <u>የአብርሃም ወንምድም ልጅ ሎጥ</u>:-ቀሳፍያን ሰብአ መላዕክት ሰዶምና ገሞራን ልናጠፋ ከእግዚአብሔር ተልከናልና ራስህን ቤተሰብህን አድን ብለው በነገሩት ጊዜ ሸሽቶ ለማምለጥ አቅም የለኝምና በፊታችሁ ወዳለችው ከተማ እስከምደርስ ታገሱኝ ብሎ ስለለመናቸው የተናገርሃትን ከተማ እንዳላጠፋት እነሆ በዚህ ነገር የለምንሽኝን ተቀብያለሁ በቶሎ ወደዚያ ሸሽተህ አምልጥ ወደዚያ እስከምትደርስ ድረስ ምንም አደርግ አንድ አልችልምና አለው:: የከተማይቱም ስም ዞአር እንደተባለ ተመዝግቧል እንደቃሉ ምልጃው በትክክል ለመፈጸሙ ያጻድቁ ሎጥ ሕይወት ከነልጆቹ ከመቅሰፍቱ ተርፏል ሚስቱ ግን የመልዕክተኞቹን

መልዕክት ባለመቀበሏ የጨው ሀውልት ሆና ቀርታለች:: ኦሪ ዘፍ ምዕ 19:ቁ.21-26

3. አብርሃም ወልደ ታራ:- የጌራራ ንጉስ አቤሜሌክ አብርሃም ወደ ሀገሩ ተሰዶ ሳለ ሚስቱን ለመድፈር በመሞከሩ እግዚአብሔር በህልም አለው ይህን በልብህ ቅንነት እንዳደረግህ አወቅሁ አሁንም የሰውየውን ሚስት መልስ ነቢይ ነውና ስለ አንተም ይጸልያል:: እንዳትነካ አንተም ከመቅሰፍት ትድናለህ ባትመልሳት ግን አንተ እንደምትሞት ከአንተ የሆነውም ሁሉ እንዲሞት በእርግጥ እወቅ ብሎ ስለነገረው አቤሜሌክም አብርሃምን በግዛቴ በወደድከው ተቀመጥ በማለቱ አብርሃምም ወደ እግዚአብሔር ጸለየ እግዚአብሔርም አቤሜሌክን ሚስቱንም ቤተ ሰቦቹንም ፈወሳቸው ይላል ታሪኩ:: ይህ የአብርሃምን ቅድስናና በእግዚአብሔር ዘንድ ያለውን ባለሟልነትና ተሰሚነት ያሳያል በጸሎቱ ባቀረበውም ምልጃ አቤሜሌክ ከእነቤተሰቡ እንዲፈወስ አድርጎታል::.

4. <u>ሙሴ ወልደ እንበረም</u>:- ዕብራውያን ወይም እሥራኤላውያን ከግብጽ ባርነት ባህር ከፍሎ ጠላት አጥፍቶ ነጻ ያወጣቸውና አርባ ዘመን መና ከደመና እያወረደ የመገባቸውን አምላክ ዘንግተው ጣዖት እያመለኩ ስለአስቸገሩት እንዲመራቸው በእነሱ ላይ የተሾመውን ሙሴን እግዚአብሔር እንዲህ ዓለው «አሁንም ቁጣዬ እንዲቃጠልባቸው እንዳጠፋቸውም ተወኝ አንተንም ለታላቅ ህዝብ አደርግሃለሁ» ስለአለው ሙሴም በእግዚአብሔር ምላክ ፊት ቁሞ ጸለየ እንዲህ በማለት አቤቱ ቁጣህ በታላቅ ኃይልና በጽኑ እጅ ከግብጽ ምድር ባወጣኸው በህዝብህ ላይ ለምን ተቃጠለ? ከመአትህ ተመለስ ለህዝብህም በክፋታቸው ላይ ራራ ዘራችሁን እንደ ሰማይ ከዋክብት አበዛለሁ ብለህ በራስህ የማልህላቸውን ባሪያዎችህን አብርሃምንና ይስሀቅን እሥራኤልንም አስብ እግዚአብሔርም በህዝቡ ላይ ሊያደርግ ስለአሰበው



መቅሰፍት ራራ ኦሪ.ዘፀ.32 ቁ.10 14 እና ቁ.32 ኦሪ.ዘኁ.ምዕ. 14 ቁ.19-20 ተመልከቱ::መልዕክቱ ሲነበብ እንደሚነግረን የእግዚአብሔር ሹም ሙሴ እንድመራው የሰጠኸኝን ህዝብ ከምታጠፋው እኔን ከጻፍከኝ ከህይወት መጽሐፍህ ብትደመስሰኝ ይሻለኛል በማለት ወደ እግዚአብሔር ስለጮኸ ጸሎቱ ተሰምቶለት ምልጃው ተፈጽሞለት ህዝቡን ከመቅሰፍት ታድጓቸዋል::

5. <u>ነቢየ እግዚአብሔር ኤልያስ</u>:- ቅዱሳን አበውና ነቢያት ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር በጸሎታቸውና በምልጃቸው የሚያስታርቁት በህይወት ሳሉ ብቻ አይደለም:: ከሞቱም በኋላ የማስታረቅና የማማለድ ሥልጣን ተሰጥቶአቸዋል ይኸውም በስራፕታ መንደር ኤልያስን ትመግበው የነበረችው ባልቴት ልጅ ታመመ ደዌውም እጅግ ከባድ ነበር:: ልጁም ከደዌው ጽናት የተነሳ ሞተ ኤልያስም የልጁን አስከሬን ተቀምጦበት ከነበረው ሰገነት አወጣው በአልጋውም ላይ አጋደመው ወደ እግዚአብሔር አቤቱ አምላኬ ሆይ የዚህ ብላቴና ነፍስ ወደ እርሱ ትመለስ ዘንድ እለምንሃለሁ ብሎ ጮኸ ጸለየ እግዚአብሔርም የኤልያስን ቃል ሰማ የብላቴናውም ነፍስ ወደ እርሱ ተመለሰች እርሱም ዳነ ተነሳ ይላል ታሪኩና መልዕክቱ ቀዳ.ነገ.ምዕ 17 ቁ.17-24 ነቢየ እግዚአብሔር ኤልያስ በዚህ መልእክት ሙት እስከማንሳት ሥልጣን ከእግዚአብሔር እንደተሰጠው እንገነዘባለን::

6. <u>ነቢየ እግዚብሔር ኤልሳዕ</u>:- ነቢየ እግዚአብሔር ኤልሳዕም የመምህሩ የኤልያስ ሀብተ መንፈስ ቅዱስ ስለ አደረበት የመምህሩን የምልጃ ሥራ ደግሞታል:: ይኸውም ኤልሳዕ ትረዳው የነበረች የሱናማዊቷ መበለት ልጅ ስለአልነበራት ልጅ እንድትወልድ ወደ እግዚአብሔር እንዲጸልይላት ነግራው በጸሎቱ ልጅ ከአስገኘላት በኋላ አድጎታሞ ስለሞተባት ወደ ኤልሳዕ ሄዳ ህያው እግዚአብሔርን በህያው ነፍስህም እምላለሁ አልተውህም

አለችው ተነስቶም ተከተላት ግያዝም ቀደማቸው እንደደ ረሰም በትሩን በህጻኑ ላይ አኖረው ነገር ግን ድምጥም ማሰማት አልነበረም:: ኤልሳዕም ወደ ቤት በገባ ጊዜ እነሆ ህጻኑ ሞቶ በአልጋው ላይ ተጋድሞ ነበር:: ገብቶም በሩን ከሁለቱ በኋላ ዘጋው ወደ እግዚአብሔርም ጸለየ ህጻኑም ዓይኖቹን ከፈተ ሴቲቱንም ጠርቶ ልጅሽ ህያው ሆኖአልና ውሰጂ አላት ገብታም ለኤልሳዕ ሰግዳ ልጇን አንስታ ወጣች ይላል ታሪኩና መልዕክቱ ካል.ዕ ነገ.ምዕ 4ቁ. 32-37 እንዲሁም ይህ ነቢይ በህይወት ሳለ ብቻ ሳይሆን ሙት ያስነሳው ከሞተም በኋላ አጽሙ ሙት አስነስቶአል:: ነገ.ካል.ምዕ.13 ቁ.20-21 ተመልከት ቅዱሳን ስንኳን በህይወት ሳሉ ከሞቱም በኋላ ከአምላካቸው በተሰጣቸው የምልጃ ቃል ኪዳን መሰረት ሰውን በቃል ኪዳናቸውና በስማቸው ከእግዚአብሔር ጋር ሲያስታርቁና ሲያማልዱ እንደሚኖሩ ይህ ህያው ታሪክና መልእክት ያስገዝበናል::

7. <u>ኢዮብ:- አርከ እግዚአብሔር</u>:- ኢዮብ እግዚአብሔርን የሚፈራ ከክፋትም ነገር ሁሉ የራቀ ፍጹምና ቅን ሰው ነበር:: በዚህም ሰይጣን ቀንቶ በአምላክ በእግዚአብሔር ፊት ነገር ለመሥራት ሞክሮ ነበር ግን ኢዮብን አካሉንና ልጆቹን እንዲሁም ንብረቱን እስከማጣት ቢያደርሰውም በፍጹም ትእግሥት ስለተዋጋው በአሸናፊነት በትዕግሥት ስለተወጠ አካሉም ንብረቱም ከመመለሱም ሌላ ልጆችም ተተክተውለታል:: በዚህም ትእግስቱ ፍጹም የእግዚአብሔር ባለሟል ስለሆነ የማማለድ ሥልጣን ከእግዚአብሔር ተሰጥቶታል:: እግዚአብሔርም ይህን ቃል ለኢዮብ ከተናገረ በኋላ ቴማናዊውን ኤልፋዝን እንደ ባሪያዬ እንደ ኢዮብ ቅን ነገር ስለ እኔ አልተናገራችሁምና ቁጣዬ በአንተና በሁለቱ ባልንጀሮችህ ላይ ነድዶአል አሁንም የሚቃጠል መስዋዕት ይዛችሁ ወደ ባሪያዬ ወደ ኢዮብ ዘንድ ሂዱ ባሪያዬም ኢዮብ ስለእናንተ ይጸልያል እኔም እንደስንፍናችሁ እንዳላደርግባችሁ ፊቱን እቀበላለሁ:: ቴማናዊው ኤ



ልፋዝም በልደጸስም ሶፋርም ሄደው የኢዮብን ፊት ተቀበለ ከሚደርስባቸው መቅሰፍትም በኢዮብ ጸሎትና ምልጃ ዳኑ:: ኢዮብ ምዕ.42 ቁ.7-9 ምሳ. ሰሎሞን ምዕ 15.ቁ.29 ወ.ዘ.ተ በዚህም ኢዮብ የእራሱን ግዳጅ ከመፈጸሙም በላይ በተሰጠው ጸጋ የባልደረቦቹን ህይወት ሊያተርፍ ችሎአል::

8. <u>ኤርምያስ ወልደ ኬልቅዮስ</u>:- ነቢየ እግዚአብሔር ኤ ርሚያስ እሥራኤላውያን በኃጢአታቸው ተፈርዶባቸው በስደት በባዕድ ሀገር ሳሉ እንዲታደጋቸው ከእግዚአብሔር የተላከ ታላቅ የእግዚአብሔር ታማኝ ነቢይ ነበር:: በዚህም ታማኝነቱ ዕብራውያን እግዚአብሔርን በበደሉ ቁጥር ወደ እግዚአብሔር በጸሎት እየአመለከተ ይቅርታ ሲያስገኝላቸው እንደነበር የራሱ መጽሐፍ በሰፊው ያስ ረዳል:: ይሁን እንጂ እነሱ እግዚአብሔርን ከማሳዘን ስለአልተመለሱ እግዚአብሔር ለኤርምያስ እንግዲህ አልሰማህምና ስለዚህ ህዘብ አትጸልይ ስለእነርሱም ልመናና ጸሎት አታድርግ አትማልድላቸውም እንዲሁም እግዚአብሔር እንዲህ አለኝ ሙሴና ሳሙኤል በፊቴ ቢቆሙም ልቤ ወደዚህ ህዝብ አያዘነብልም ከፊቴ ጣላቸው ይውጡ በማለት እንደአነጋገረውና የባለሟልነቱንም ሥራ በትክክል እንዲፈጽምና እንደሚያስፈጽም መልእክቱ ያስገነዝባል:: አ.ር.ምዕ.7 ቁ.16 ምዕ.15 ቁ.1 እናም ምዕ.42 ቁ. 2-11 ተመልከት::

9. <u>ሄኖክ ወልደ ያሬድ</u>:- ይህ ሰው መራራ ሥጋዊ ሞትን ያልቀመሰ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ያደረገ ታላቅ ሰው እንደነበር ቅዱስ መጽሀፍ ያስገነዝበናል:: ይህ ታላቅ ሰው ቅዱሳንን ሰዎች ከሞተ ሥጋም በኋላ በአፀደ ነፍስ እያሉ በምድር ላሉ ህያዋን እንደሚጸልዩ ከዚያ ቦታ ዓይኖቼ ከመላእክት ጋር የሚኖሩበት ማደሪያቸውን ከቅዱሳንም ጋር የሚኖሩበት ቦታቸውን አዩ:: ስለሰውም ልጆች ፈጽመው ይለምናሉ ይጸልያሉ በማለት ጽፎአል:: ሄኖክ ምዕ.9 ቁ.23 ራዕ.ምዕ.6 ቁ.9-11 ወ.ዘ.ተ

ከላይ በአጭሩ እንደተገለጸው የብሉይ ኪዳን ምልጃና ዕርቅ እንዴት እንደተፈጸመ በበቂ ማስረጃ ተመልክተናል:: ቀጥሎ ደግሞ በሐዲስ ኪዳን የተፈጸመውንና በመፈጸም ላይ ያለውን ምልጃና ዕርቅ እንመለከታለን::

## ፀ. ለ. <u>በሐዲስ ኪዳን የቅዱሳን ምልጃና ዕርቅ አፈጻጸም</u>

በአዲስ ኪዳን የቅዱሳንን የማማለድና የማስታረቅ ሥራ ከመመልከታችን በፊት የሀዲስ ኪዳን መሥራችና ፈጻሚ የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ለሰው የአደለውን ስጦታና ሀብት በአጭሩ እንመለከታለን:- ይኸውም ጌታችን ሰውን ከመርገምና ከፍርድ ለማዳን ሰው ስለሆነ ከኃጢአት በቀር ሰው ሊሰራው የሚገባውን ማናቸውንም በጎ ሥራ ሰርቶአል:: ስለሆነም ተጠምቆአል ጾሟል ጸልዮአል ታርቆአል አስታርቆአል::

ሀ. ለምን ተጠመቀ? ልጅነት ክብር አጥቶ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ቅዱብ ልጅነትና ክብር ለማግኘት ነውን? እርሱ ማን ሆኖ ከሥላሴ አንዱ አካል የባህርይ አካል አይደለምን? ወደ ዓለም የመጣውና ሰው ለመሆን ያበቃው ይህን ልጅነትና ክብር ለሰው ለመስጠት አይደለምን? የተጠመቀውም ለሰው ሥርዓተ ጥምቀትን ለመመሥረት ነው::

ለ. ለምን ፆመ? በደል ኖሮበት ከኃጢአት ለመንጻት ነውን? ወይስ እንደሌላው ፍጡር ሰው ደካማ ሆኖ በጾም ኃይል አግኝቶ ዲያብሎስን ድል ለማድረግና በድል አድራጊነቱ ሊጸድቅ ነውን? እርሱ ድል አድራጊ የባህርይ አምላክ አይደለምን?

ሐ.ለምን ጸለየ? ጸሎት እኮ ለደካማ ፍጡር ሰው ከፈጣሪ ኃይል ለማግኘትና ፍላጎትን የማርኪያ ሥልትና መንገድ ነው:: ክርስቶስ ምን አጥቶ ምን ጎድሎበት ነው በጸሎት ለመጠቀም የሞከረው ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ኃይልን አግኝቶ ሥጋዊ ፍላጎቱን ለማርካት ነውን? ወይስ በዲያብሎስ ከሚወረወረው ጦር ለመከላከል አስቦ ነው እርሱም ጸሎትን ተቀባይ እንጂ በጸሎት ከጠላት ለመከላል



የሞከረ ደካማ ፍጡር አይደለም:: እርሱ ኃያልና የባህርይ አምላክ የኃይል ባለቤት ነው:: ይህን መገንዘብ አለብን::

መ. ለምን ማለደ? በአዳምና በሔዋን አለመታዘዝ የተነሳ በሰው ልጆች ላይ ሁሉ የደረሰው የሥላሴ ልጅነትን የማጣት መርገም ደርሶበት ከዚያ መርገም ለመዳን እግዚአብሔርን መለመን ግድ ሆኖበት ነውን? በዚህ ጉዳይ እርሱ እራሱ ተማላጅ ታራቂ አይደለምን? ምክንያቱም እርሱ እራሱ የባህርይ አምላክ ነውና::ታድያ እነዚህን ጥምቀትን ጾምን ጸሎትን ምልጃን ለእራሱ ካልተ ጠቀመባቸው ለምን በተግባር ፈጸማቸው የሚል አመለካከት ካለ መልሱ ቅርብ ነው:: እግዚአብሔር ወልድ ሰውን ለማዳን ሰው በሆነ ጊዜ ለማዳን ሥራው ሰዎችን ከሰው መርጦ ለመጣበት ዓላማው አስልጥኖአል:: በመሆኑም መጠመቅ መጸለይ ወይም መማለድ የመረጣቸውና ወደ ዓለም እንዲያስተምሩ የላካቸው ሥራዎች ስለሆኑ እንዲጠመቁ እንዲጾሙ እንዲጸልዩ ከእምነት ጋር እንዲሰሩ ለማስተማር የተጠቀመበት ትምህርትና መመሪያ ለመስጠት መሆኑን መገንዘብ ይገባናል::

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እነዚህን የሰራቸው በመዋዕለ ትምህርቱና በመዋዕለ ሥጋዌው ከዕለተ ዓርብ ከስቅለት በፊትና ከዕርገት በፊት የፈጸማቸው ለማስተማር ስሆነ አሁን በእርሱ ዘንድ ተቋርጠዋል:: የማማለድና የማስታረቅንም ሥራ ለቤተ ክርስቲያንና ለቅዱሳን አስረክቦአል:: እርሱ የባህርይ አምላክ ነውና አሁን እርሱ በጥምቀቱ በስሙ በመስዋዕቱ አማካይነት የሚቀርብለትን ጾም ጸሎት ምልጃን /ዕርቅን/ተቀባይ ሆኖአል::

ይህንንም እንደሚከተለው በተጨባጭ ማስረጃ እንመለከታለን::

1. አንሰ ሰባሕኩከ በዲበ ምድር ፈጺምየ ግብረ ዘወሀብከኒ ከመ እግበር እኔ ላደርገው የሰጠኸኝን ሥራ ፈጽሜ በምድር አከበርሁህ::ዮሐ.ምዕ.17 ቁ.4 በዚህ ቃል መሰረት ክርስቶስ

የመጾም የመጸለይ የማማለድ ሥራውን ፈጽሞአል/ ጨርሶአል/ አሁን ለአብነት ይሰራው የነበረው ሥራው ለቤተ ክርስቲያንና ለቅዱሳን ተሰጥቶአል፡፡ዛሬ ክርስቶስን ጹምልን ጸልይልን አማልደን ማለት የግብዞች ቋንቋ ነው፡፡ እርሱ ጾምን ጸሎትን ምልጃን ተቀብሎ ዋጋ ከፋይ ነው፡፡ ከዚህ ውጭ ክርስቶስን ወደ ፍጡር መንተት የዋህነት ነው፡፡ ልንጠነቀቅም ይገባል አያዋጣም፡፡

2. ወእመቦ ዘሰአልክሙ በስምየ እገብር ለክሙ ኪያሁ ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ በ ማለት የምልጃንና የማስታረቅን ሥራ በዚህ ሕያው ቃሉ ለቤተክርስቲንና ለቅዱሳን ማስረከቡን ቃሉ ያስገነዝበናል፡፡ ጌታችን ለምኑ! እኔም አደርገዋለሁ አለ እንጂ ከአብ ዘንድ አስፈጽምላችኋለሁ እንዲፈጸምላችሁ አደርጋለሁ አላለም፡፡ እኔው አደርገዋለሁ ነው ያለው አምላክ ነውና የማድረግ ኃይልና ችሎታ አለውና፡፡ ዮሐ.14 ቁ.14

3. ወይእተ አሚረ ትሰእሉ በስምየ ወኢይብለክሙ ከመ አነ ዘእስእሎ ለአብ በእንቲአክሙ :- በዚያን ጊዜ በስሜ ትለምናላችሁ እኔም ስለ እናንተ አብን እንድለምን የምላችሁ አይደለሁም፡፡ ዮሐ.ምዕ16 ቁ.26 እንግዲህ ከአሁን በኋላ በስሜ ትለምናላችሁ እኔ ከአሁን በኋላ ስለእናንተ አብን የምለምን አይደለሁም፡፡ እኔና አብ አንድ ነን ባለው ቃል መሰረት ዮሐ.10 ቁ.30 አሁን ክርስቶስ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ዝቅተኛ ሆኖ አብን ስለሰው ጉዳይ የሚለምን አለመሆኑን በህያው ቃሉ አረጋግጦአል፡፡ ከዚህ አምላካዊ ቃል ማስረጃ ውጭ ክርስቶስ ያማልዳል ማለት የክርስቶስን የባህርይ አምላክነት አለማመንና የግንዛቤ ማነስ ካልሆነ በቀር ፍጹም የዋህነት ነው፡፡ ልንጠነቀቅም ይግባል፡፡

4. ወእስከ ይእዜሰ ኢሰአልክምዎ ለአብ ወኢምንተኒ በስምየ ስአሉ ወተነሰኡ ከመ ፍጹመ ይኩን ፍሥሐክሙ እስከ አሁንበስሜ ምንም አለመናችሁም ደስታችሁ ፍጹም



እንዲሆን ለምኑ ትቀበላላችሁ፡፡ ዮሐ.ምዕ. 16 ቁ.24 ዮሔ.ምዕ 17 ቁ.17-18 ወ.ዘ.ተ ተመልከቱ፡፡

ከላይ ከ1-4 ተራ ቁጥር ለማስረጃ ያህል አጠር ባለ መልኩ እንደተገለፀው ዛሬ የባህርይ አምላክ ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያንና የቅዱሳንን ምልጃን ጸሎት ተቀባይ እንጂ አማላጅ አይደለም፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ሲገሥፀን ማንም እንደቆመ የሚመስለው ቢኖር እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ እንዳለ ራሳችንን አሳስተን ከእግዚአብሔር መንግሥት እንዳንወጣ ከመሳሳት እንጠንቀቅ፡፡

እንግዲህ ከዚህ በላይ እንደተገለፀው አምላካዊ ፈቃድ መሰረት በጥምቀቱ በስሙ እራሱ ለሰው ድህነት በአቀረበው በሥጋውና በደሙ መስዋዕት መታረቂያነት እስከ ፍጻሜ ድረስ ለሚነሱ ሰዎች ራሱ ጌታችን በሰጠው የማማለድና የማስታረቅ ሥልጣን ቤተክርስቲያንና ቅዱሳን እንዴት እንደተጠቀሙበት በማመልከት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማሥራጃዎችን እንመለከታልን:-

1. ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ወናሁ ኮነ ኩሎ ሐዲስ እምኀበ እግዚአብሔር ዘአቅረበነ ኀቤሁ በክርስቶስ ወወሀበነ መልእክተ ሥምረቱ ወረሰየ ሳዕሌነ ቃለ ሥምረቱ ወወሀበነ መልእክተ ሳህሉ ወንህነሰ ንትንበል በአለምሳለ ክርስቶስ ወይሁበክሙ እግዚአብሔር ፍሥሐ በላዕሌነ ወ.ዘ.ተ ይህ ወደ አማርኛ ሲተረጎም ነገር ግን የሆነው ሁሉ በክርስቶስ ከራሱ ጋር ከአስታረቀን የማስታረቅም አገልግሎት ከሰጠን ከእግዚአብሔር ነው ይልና በእኛም የማስታረቅ ቃል አኖረ፡፡ እንግዲህ እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማለድ ስለክርስቶስ መልእክተኞች ነን፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን ስለክርስቶስ እንለምናለን፡፡ 2ኛ.ቆሮ.ምዕ 5 ቁ.18-20 በማለት የማማለድና የማስታረቅ ሥልጣን ለቅዱሳንና ለቤተ ክርስቲያን እንደተሰጠ አረጋግጦአል፡፡

2. አኮ በእንተ ዝንቱ ባህቲቱ ዓዲ ንተሜካህ በኀበ እግዚአብሔ ር በእንተ እግዚኢነ ኢየሱስ ክርስስ ዘበእንቲአሁ ረከብነ

ማህሎ ይህ ብቻ አይደለም ነገር ግን አሁን መታረቁን በአገኘ ንበት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በእግዚአብሔር ደግሞ እንመካለን:: ሮሜ ምዕ.5 ቁ.11 በዚህም መልእክቱ የመታረቅና የማስታረቅ ሥልጣን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በመገኘቱና በመፈቀዱ በእግዚአብሔር እንመካለን በማለት ሐዋርያው መስክሮአል::

3. አማን እብለክሙ ዘአሰርክሙ በምድር ይከውን እሱ ረ በሰማያት ወዘፈታህክሙ በምድር ይከውን ፍቱሐ በሰማያት ማቴ.ምዕ.ቁ18ወደ አማርኛ ሲተረጎም እርሱ እራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እውነት እላችኋለሁ በምድር የምታስሩት ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል በምድርም የምትፈቱት ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል:: በማለት ለተ ከታዮቹ ቅዱሳን ሐዋርያት የማሰርና የመፍታት ሥልጣን ሰጥቶአቸዋል:: ይህ ሥልጣን ከፍተኛ ነው:: አግዚአብሔርን ወክሎ በእግዚአብሔር ምድራዊ መንግሥትና ሰማያዊ መንግሥት የሚሰራ ሥልጣን ስለሆነ በቀላሉ የሚታይ አይደለም::

4. ወኵሎ ዘሰአልክሙ በጸሎት እንዘትትአመኑ ትነስኡ አምናችሁም በጸሎት የምትለምኑትን ሁሉ ትቀበላላችሁ ኣላቸው:: ማቴ.ምዕ. 21 ቁ.22 ማር.ምዕ. 11 ቁ.24 ስለዚህ ነው ዛሬ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ክርስቶስ በጸሎት የቀ ረበ ምልጃን ይቀበላል እንጂ ዛሬ እርሱ ለማንም አይጸልይም አይማልድምም የተባለው:: ምክንያቱም በዚህ ቃሉ ጸሎትና ምልጃን ለቅዱሳንና ለቤተክርስቲያን አስ ረክቦአልና ነው:: ይህን ፈቃድ ከአምላኳ ስለአገኘች ነው ዛሬ ቤተክርስቲያን ሐያ አራት ስዓት ለፈጣሪዋ በምታ ቀርበው በጸሎቷ በቅዳሴዋ በዝማሬዋ ስለህሙማን ስለህያዋን ስለሙታን ስለዝናም ስለፍሬ ምድር ስለመከር ስለማያተ አፍላግ/ስለወንዞች/ ስለሀገር ስለሰላም አማላጅነቷን አውቃ ሳታቋርጥ ስትጸልይ ስታማልድ የምትኖረው::

5. ወእመበ ዘሰአልክሙ በስምየ እገብር ለክሙ ኪያሁ



ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ:: የሐ.ምዕ.14 1ኛ ዮሐ.ማል .ምዕ 5 ቁ.17 ከዚህ ህያው ቃል የበለጠ ለሰው ልጅ ፈቃድና ሥልጣን የለም:: የመለመንና የማማለድ የማስታረቅን ሥልጣን ክርስቶስ ለቅዱሳን ስጥቶአል ከዚህ ውጭ ክርስቶስን አማላጅ ነው ማለት በክርስቶስ ማፌዝ ነው:: አያዋጣም ልንጠነቀቅ ይገባል::

6. ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለፊልጲስዩስ ሰዎች ሲጽፍ በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችሁን አስታወቁ እንጂ በአንዳች አትጨነቁ በማለት ጸሎትና ምልጃ በሰው በኩል እንዲፈጸም እግዚአብሔር ስለፈቀደ አትጨነቁ ሥልጣን ተ ሰጥቶናል ሲል አረጋግጦአል:: ፊሊ.ምዕ4 ቁ.6 1ኛ.ተ ሰ.ምዕ.5 ቁ.17 ያዕ.ምዕ.5 ቁ15 ወ.ዘ.ተ እነዚህ ሁሉ ማስ ረጃዎች የቤተክርስቲያን ካህናትና ቅዱሳን ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር በጸሎታቸው ሲያማልዱና ሲያስታርቁ ያሳዩሀልና በማስተዋል አንባቸው ከስህተ ትም ትድናለህ::

እግዚአብሔር ለቅዱሳን የሰጣቸው ሀብትና ሥልጣን በጸሎታቸውና በትሩፋታቸው ሰውን ከራሱ ጋር አማልዶ ማስታረቅ ብቻ አይደለም:: በርኩሳን መናፍስት በአጋንንትና በደዌ እንዲሁም በሞት ላይ የመፈወስና የማዳን ኃይል ሰጥቶአቸዋል:: ይህንም ሀብትና ሥልጣን በሚከተለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ ሳይባዛ እንመለከታል:-

## ሀ. በአጋንንት ላይ የተሰጠ ሥልጣን

ለሐዋርያት ድውዮችን ፈውሱ ሙታንን አንሱ ለምጻሞችን አንጹ አጋንንትን አውጡ ብሎ ማቴ.ምዕ.10 ቁ.8 ጌታችን ኢየሱስ ክስቶስ በፈቀደው መሰረት

1. ሰብዓውም አርድዕት በደስታ ተመልሰው:- ጌታ ሆይ

አጋንንት ስንኳን በስምህ ተገዝተውልናል አሉት ሉቃ.ምዕ.10 ቁ.17-18

2. ደግሞም በኢየሩሳሌም ዙርያ ከአለችው ከተማ ድውያንንና በርኩሳን መናፍስት የተሰቃዩትን እየአመጡ ብዙ ሰዎች ይሰበሰቡ ነበር ሁሉም ይፈወሱ ነበር:: የሐ.ሥራ.ምዕ.5 ቁ.16

3.ጳውሎስ ግን ተቸገረና ዘወር ብሎ መንፈሱን ከእርሰዋ እንድትወጣ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አዝዛለሁ አለው:: በዚያም ሰዓት ወጣ የሐ. ሥራ ምዕ.16 ቁ.18

4. እግዚአብሔር በጳውሎስ እጅ የሚያስገርም ታምራት ያደርግ ነበር:: ስለዚህም ከአካሉ ጨርቅ ወይም ልብስ ወደ ድውዮች ይወስዱ ነበር:: ደዌያቸውም ይለቃቸው ነበር:: ክፉዎች መናፍስትም ይወጡ ነበር:: የሐ.ሥራ ምዕ. 19 ቁ.11-13 ወ.ዘ.ተ ተመልከቱ::

## ለ. በደዌ ላይ የተሰጠ ሥልጣን

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ድውያንን ፈውሱ ብሎ በሰጠው ሀብትና ሥልጣን መሰረት:-

1. ጴጥሮስና ዮሐንስ በ9 ሰዓት መልካም ወደሚሏት ቤተ መቅደስ ለጸሎት ሲገቡ ከእናቱ ማኅጸን ጀምሮ አንካሳ የሆነ አንድ ሰው ነበር:: እርሱም ጴጥሮስንና ዮሀንስን አይቶ ምጽዋት ለመናቸው:: ጴጥሮስም ወደ እኛ ተመልከት አለው ድኃውም አንዳች ነገር ይሰጡኛል ብሎ ይጠብቅ ነበር:: ጴጥሮስ ግን ብርና ወርቅ የለኝም ይህን ያለኝን ግን እስጥሃለሁ በናዝሬቱ ኢየሱስ ስም ተነሳና ተመላለስ አለው በቀኝ እጁም ይዞ አስነሳው በዚያን ጊዜም እግርና ቁርጭምጭሚቱ ጸና ወደ ላይም ዘሎ ቆመ ይመላለስም ጀመር እግዚአብሔርንም እየአመሰገነ ከእነርሱ ጋር ወደ መቅደስ ገባ የሐ.ሥራ.ምዕ3 ቁ.4-10
2. ጴጥሮስ በማስተማር ልዳ በምትባል ሀገር በደረሰ ጊዜ በዚያም ከስምንት ዓመት ጀምሮ በአልጋ ላይ ተኝቶ የነበረውን ኤንያ የሚሉትን አንድ ሰው አገኘ እርሱም ሽባ ነበረ:: ጴጥሮስም ኤንያ ሆይ ኢየሱስ ክርስቶስ ይፈውስሃል



ተነሳ ለራስህም አንጥፍ አለው ወዲያውም ተነሳ:: የሐ.ሥራ.ምዕ 9 ቁ.32-34

3. እግዚአብሔርም በጳውሎስ እጅ የሚያስገርም ታምራት ያደርግ ነበር ስለዚህም ከአካሉ ጨርቅ ወይም ልብስ ወደ ድውዮች ይወስዱ ነበር ደዌያቸውም ይለቃቸው ነበር የሐ ሥራ.ምዕ 19 ቁ.11-12
4. በሐዋርያትም እጅ ብዙ ምልክትና ድንቅ በሕዝብ መካከል ይደረግ ነበር ስለዚህም ጴጥሮስ ሲያልፍ ጥላውም ቢሆን ከእነርሱ አንዱን ይጋርድ ዘንድ ድውያንን ወደ አደባባይ አወጥተው በአልጋና በወሰካ ያኖሩአቸው ነበር:: ሁሉም ይፈወሱ ነበር:: የሐ.ሥራ.ምዕ19 ቁ.12-16 ያዕ. ምዕ.5 ቁ.14-15 ተመልከት

## ሐ. በሞት ላይ የተሰጠ ሥልጣን

እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ለቅዱሳን ምርጦቹ የሰጣቸው ሀብት ማማለድና ማስታረቅ አጋንንትን ማውጣትና ድውያንን መፈወስ ብቻ አይደለም በሞትም ላይ ሥልጣን ሰጥቶአቸዋል ለአብነት ያህል የሚከተሉትን ማስረጃዎች መመልከት ይበቃል::

1. እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በኤልያስ አድሮ አንድ ምውት አስነስቶአል ይህም የኤልያስ ሥልጣንና ክብሩ ነው ለመንፈስ ቅዱስ መሳሪያ ሆኖ በመገኘቱ ነገ.ቀዳ.ምዕ 17 ቁ.23
2. እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በኤልያስ ደቀ መዝሙር በኤልሳዕ አድሮ ሁለት ምውታን አስነስቶአል ይህም የኤልሳዕ ሥልጣንና ክብሩ ነው ለመንፈስ ቅዱስ መሳሪያ ሆኖ በመገኘቱ ነገ.ካል.ምዕ 4 ቁ.32 እናም ምዕ 13ቁ.20-21
3. እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያው በቅዱስ ጴጥሮስ አድሮ አንድ ምውት ደርቃን ከሞት አስነስቷል የመንፈስ ቅዱስ መሳሪያ ሆኖ በመገኘቱ የሐ ሥራ.ምዕ 9 ቁ36-41 ወ.ዘ.ተ ተመልከት ይህ ለጴጥሮስ ከመንፈስ ቅዱስ የተሰጠ ሥልጣንና ክብሩ ነበር ይህ ሙት የማስነሳትና አጋንንት

ወጡ ሙታን ሲነሱ ድውያን ሲፈወሱ ይታያል ሰው የእግዚአብሔር ከሆነ እግዚአብሔር ጋር መኖር መርጦ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ከሰራ የሚሳነው ነገር የለም እርሱ ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእኔ የሚያምን እኔ የምሰራውን ሥራ ይሰራል ከዚያም የበለጠ ይሰራል ብሎ ተናግሮአልና ነው ዮሐ.ምዕ.14 ቁ.12 ወ.ዘ.ተ ተመልከት በመሰረቱ ሰው በተፈጥሮው ደካማ ፍጡር መሆኑን እናውቃለን ስንኳ ን ሌላውን ማዳን ቀርቶ ራሱንም ማዳን የማይችል መሆኑን በውል እንገነዘባለን ታዲያ ሰው እንዲህ ከሆነ በአጋንንት ላይና በሞት ላይ እንዴት ሥልጣን ሊኖረው ቻ ለ? የሚለውን ጥያቄ ሊፈጥርብን ይችላል በእርግጥም አጠያያቂ ነው ምክንያቱም ሰው ከሞተ ነፍሱ ከስጋው ከተለየች በኋላ ነፍስን ከአለችበት ከአፀደ ነፍስ አምጥቶ ከበድን ሥጋ ጋር አዋህዶ ማስነሳት አጋንንት ሥጋ የላቸውም ረቂቃን ናቸው ሰው ግን ግዙፍ ነው ረቂቃኑን ከግዙፍ ሥጋ እንዲለዩ ማድረግ እንዴት ይቻላል? ለሚል ጠያቂ መልሱ ጌታችን ለሚያምን ሁሉ ይቻላል ብሎአልና ማር.ምዕ 9ቁ.23 ሰው ራሱን ክዶ አምላኩን ከተከተለ ከአምላክ ጋር ለመስራት ከወሰነ በቂ ሥልጣን ይሰጠዋል:: አብሮት የሚሰራው መንፈስ ቅዱስ ከእርሱ ጋር በሚሰራው ሰው አድሮ ሥራውን ይሰራዋልና ነው:: ስለሆነም ነው ቅዱሳን ራሳቸውን ክደው መስቀል ተ ሸክመው ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ህይወታቸውን ለመምራትና ለመስራት ስለወሰኑ በሞትና በአጋንንት ላይ እንዲሁም በደዌ ላይ ሥልጣን ያገኙት ይህ አምላካዊ ሀብት የተገኘው የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ሰራተኛ ስለሆኑ ነው:: በመሆኑም ነው ሰውና እግዚአብሔርን በፀሎታቸው በትሩፋታቸው በገድላቸው ለማስታረቅ የበቁት እንዲህም በመሆኑ እግዚአብሔር በምድራዊ ሥጋዊ ህይወታቸውም ሆነ በአፀደ ነፍስና በቀጣይ ህይወት በመንግስቱ የማይለወጥና የማይጠፋ ክብርና ስም የሰጣቸው::

# ምዕራፍ 7



## የቅዱሳን መታሰቢያ

ቅዱሳን ኃያል አምላክ እግዚአብሔር እንደጠራቸው እንደመ ረጣቸው እንደአከበራቸው ክርስቶስ ለሞተለት ለሰው ልጆች ህይወት ለማዳን ሥራው እንደላካቸው ያስታጠቃቸውና የሰጣቸው ሰማያዊ የኃይል ሀብት አጋንንትን የማውጣት ደዌያትን የመፈወስ ሙታንን የማስነሳት በደለኛን ከፈጣሪው ጋር የማማለድና የማስታረቅ ሥልጣን ብቻ አይደለም:: ብሉይ ኪዳንና ሐዲስ ኪዳን መጻህፍት እንዲሁም የራሳቸው ሥራ ገድላቸው እንደሚመሰክረው የማይጠፋ የማይለወጥና የማይሻር የዘለዓለም መታሰቢያ በቤቱ በቤተ መቅደስ በቤተእግዚአብሔር ስማቸው ተተክሎ እንዲኖር በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነት ያመነ ሁሉ ሰማቸውን እየጠራ አምላኩን እንዲማፀን አፅማቸው በአረፈበት ቅዱስ ቦታ በመገኘት የገድላቸውና የቃል ኪዳናቸው ተካፋይ እንዲሆን እግዚአብሔር መታሰቢያቸው እንዳይጠፋ ህያው ሆኖ እንዲኖር ፈቅዶላቸዋል:: ይህንንም በሚከተሉት ማስረጃዎች መገንዘብ ይቻላል::

### ሀ. የቅዱሳን መታሰቢያ በብሉይ ኪዳን

1. እግዚአብሔር አብርሃምን አለው ከአገርህ ከዘመዶችህም ከአባትህም ቤት ተለይተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር ውጣ ታላቅ ህዝብም አደርግሃለሁ እባርክሃለሁ ስምህንም አከብ ረዋለሁ ለበረከትም ሁን የሚባርኩህንም እባርካለሁ የሚ ረግሙህንም እረግማለሁ የምድር ነገዶችም ሁሉ በአንተ ይባረካሉ:: ኦሪ ዘፍ.ምዕ 12 ቁ.1-3 ስምህን አከብረዋለሁ ለበ ረከት ሁን ከዚህ የሚበልጥ ስጦታ የለም ከዚህ የሚበልጥ በረከትም የለም:: ከዚህ የሚበልጥ መታሰቢያ የለም ከዚህ የሚበልጥ ቃል ኪዳን የለም ተናገሪው ህያው እግዚአብሔር ነውና ቃሉ አይለወጥምና ስለሆነም ነው ቤተክርስቲያን 24 ሰዓት በቤተበመቅደስ በእንተ አብርሃም ፍቁረከ መሐር ወስ ረይ ኃጢአተ ህዝብከ ለአብርሃምና ለዘሩ እስከ ዘለዓለም አደ ረገዋለሁ ያልከውን አስብ እያለች የምትፀልየው::

2. ዝክረ ጻድቅ ለዓለም ይሄሉ ወኢይፈርህ እምነገር እኩይ የጻድቅ መታሰቢያ ለዘለዓለም ይኖራል ከክፉ ነገርም አይፈራም:: መዝ 11 ቁ.6 ምሳሌ ምዕ 10 ቁ.30 ተመልከት የጻድቅ መታሰቢያ ለዘላለም ይኖራል አዎ! ይኖራል ለዘለአለም ህያው ሆኖ የሚኖር እግዚአብሔር ፈቅዶአልና ዘለዓለም የሚለው ቃል የእግዚአብሔር ገንዘብ ነው ፍጡር እግዚአብሔር ካላፈቀደ ዘለዓለም መኖር አይችልምና ስለሆነም ፃድቃን እግዚአብሔር ስለመረጣቸውና እነሱም በስራቸው እግዚአብሔርን ስለገለጡትና ስለአስከበሩት ለዘለዓለም የማይጠፋ ስምና ክብር ሰጥቶአቸዋል::
3. ክቡር ሞቱ ለጻድቅ በቅድመ እግዚአብሔር የጻድቅ ሞት በእግዚአብሔር ፊት የከበረ ነው:: መዝ 115 ቁ.6-15 አዎ የከበረ ነው ቅዱሳን ጻድቃን ሞታቸው የክብር እንጂ የውርደት አይደለምና ሞትን በሥራቸውና በእምነታቸው አሸንፈውታልና ሞትን ድል የነሱ የክርስቶስ ልጆች ናቸውና ሞት አላሸነፋቸውም አያሸንፋቸውምም እግዚአብሔር በእምነታቸውና በሥራቸው ስለወደዳቸው ህያዋን ፍጥረታት ናቸው ዘለዓለም ህያው ሆነው ከብረው ይኖራሉ::
4. እግዚአብሔር ሰንበቴን ለሚጠብቁ ደስ የሚያሰኘኝንም ነገር ስለሚመርጡ ቃል ኪዳኔንም ስለሚይዙ ጃንደ ረቦች እንዲህ ይላልና በቤቴና በቅጥሬ ውስጥ ከወንዶችና ከሴቶች ልጆች ይልቅ የሚበልጥ መታሰቢያና ስም እሰጣች ኋለሁ የማይጠፋም የዘለአለም ስም እሰጣቸዋለሁ:: ወደ ተቀደሰ ተራራዬ አመጣቸዋለሁ በጸሎቴም ቤት ደስ አሰኛቸዋለሁ ኢሳ.ምዕ 56 ቁ.4-7 ተመልከት ጃንደረባ ማለት ትርጉሙ በአለሚል ማለት ነው አንባቢ ሆይ አስተውል ከዚህ የሚበልጥ

መታሰቢያ ከዚህ የሚበልጥ ቃል ኪዳን የለም ጸሐፊው ነቢዩ ኢሳይያስ እንደመዘገበው ተናጋሪውና ለቅዱሳንና ለቅዱሳት በቤ ቱ በቤተ መቅደስ ስማቸው እንዲጠራ ክብር የሰጠው የዓለም ፈጣሪና መጋቢ እግዚአብሔር ነው:: ሌላ አይደለም::



በዚህ ቃሉና ፈቃዱ እግዚአብሔር ቅዱሳን ወንዶች ልጆቹንና ቅዱሳት ሴቶች ልጆቹን በቤቱ በቤተ መቅደስ ለዘለዓለም ከእርሱ ጋር ስማቸው እንዲጠራ ልጆቻቸውንም ለዘለዓለም በስማቸው እንዲማፀኑና ከእነሱ በረከት እንዲያገኙ ፈቅዶአል:: የእግዚአብሔር ቃል አይለወጥም ሕዝ.ምዕ 12 ቁ.25

ይህን ፈቃድ ይዛ ነው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የቅዱሳንና የቅዱሳት ስም በቤተ እግዚአብሔር በቤተ መቅደስ ዘወትር የምትጠራውና በስማቸው ወደ ፈጣሪዋ ስትማጸን የምትኖረው ነገሩና እውነቱ ያልገባቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም የተዘጋባቸው መናፍቃን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከፈጣሪ የታዘዘችውን በመፈጸሟ ከፈጣሪ ውጭ ሰው እንደምታመልክ አስመስለው ሲናገሩና ሲተቹ ይሰማል:: ተ ሳስተዋል ሊታረሙና ሊያጤኑም ይገባቸዋል የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከፈጣሪ ከስላሴ ውጭ ሰው አታመልክም ሰው አምልኩ ብላም አታስተምርም::

ነገር ግን ከፈጣሪ በታዘዘችው መሰረት እግዚአብሔር ያከበራቸውን ታከብራለች ታስከብራለችም እግዚአብሔር ያከበራቸውን ቅዱሳንንም በማክበሯ በበረከታቸው ስትጠቀም ትኖራለች እውነቱ ይህ ብቻ ነው:: ከዚህ ውጭ የማያውቁትን መንቀፍና መተቸት ግን ከእግዚአብሔር ጋር የሚጣሉ ይደቃሉ የሚለውን ቅጣት ይቀበላሉ 1ኛ ሳሙ.ምዕ. 2ቁ.10

## ለ. ለቅዱሳን የተሰጠ የሐዲስ ኪዳን መታሰቢያ

ልዑል አምላክ እግዚአብሔር ወልድ ሰውን ከመረገምና ከኩነኔ ለማዳን ሰውም ከሆነ በኋላ ለተከታዮቹ ለሐዋርያትና ለሌ ሎቹም ቅዱሳን ጻድቃን የማይለወጥና የማይሻር ለዘለዓለም ሕያው ሆኖ የሚኖር ቃል ኪዳንና መታሰቢያ ሰጥቶአቸዋል ይህንም በሚከተሉት አምላካዊ ቃል ማስረጃዎች ልንገነዘብ እንችላለን::

1. እነ ኀረይኩክሙ ወሜ ምኩክሙ ወእሬስየክሙ ከመ ትሁሩ ውፍሬ ትፍረዩ ወውዕቱ ፍሬክሙ ይነበር ለዓለም ከመ እመቦ ዘሰአልክምም ለአብ በስምየ ኩሎ ይሁብክሙ:: ይህ ሲተረጎም እኔ መርጬ ሾምኩአችሁ ሄዳችሁ ፍሬ ታፈሩ ዘንድ ፍሬአችሁም ለዘለዓለም ይኖራል በስሜ አብን የለመናችሁት ከአለ አብ ሁሉን ይሰጣችኋል ዮሐ ምዕ. 15 ቁ.16 ሰዎች በክርስቶስ የባህርይ አምላክነት አምነው የታዘዙትን ሰርተው ከተገኙ ሥራቸው የማይጠፋ ህያው ሆኖ ይኖራል:: ከስራቸውም ህያውነት የተነሳ እነርሱም ህያዋን ሆነው እንደሚኖሩ ክርስቶስ በዚህ ቃሉ ውል ገብቶላቸዋል:: ቃሉ አይለወጥም::
2. ዘኪያክሙ ተወክፈ ኪያየ ተወክፈ ወዘኪያየ ተወክፈ ተ ወክፎ ለዘፈነወኒ:: ዘተወክፈ ነቢየ በስመ ነቢይ ዐስበ ነቢይ ይነስእ ወዘተወክፈ ጻድቀ በስመ ጻድቅ ዓስበ ጻድቅ ይነስዕ ወዘአስተየ ለአሀዱ እምእሉ ንዑሳን ጽዋዐ ማይ ቁሪር ባህቲቶ በስመ ረድዕየ አማን እብለክሙ ኢየኀጉል ዐስቦ:: ይህ ሲተረጎም እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል እኔንም የሚቀበል የላከኝን ይቀበላል ነቢይን በነቢይ ስም የሚቀበል የነቢይን ዋጋ ይወስዳል ጻድቅንም በጻድቅ ስም የሚቀበል የጻድቁን ዋጋ ይወስዳል:: ማንም ከነዚህ ከታናናሾቹ ለአንዱ ቀዝቃዛ ጽዋ ውኃ ብቻ በደቀመዝሙር ስም የሚያጠጣ እውነት እላችኋለሁ ዋጋው አይጠፋበትም ማቴ.ምዕ 10 ቁ.40-42 ማር.ምዕ 9 ቁ.37 ቁ.41 ሉቃ.ምዕ 10 ቁ.16 ዮሐ.ምዕ 13 ቁ.20 ወ.ዘ.ተ ተመልከት ከዚህ የበለጠ መታሰቢያ የለም ምክንያቱም እኔን የተቀበለ እናንተን ይቀበላል እናንተንም የተቀበለ እኔን ይቀበላል በማለት በማይታበል ቃሉ የማይሻርና የማይለወጥ መታሰቢያ ስጥቶአቸዋል ማንም አማኝ እናንተ የክርስቶስ ናችሁ ብሎ በነቢይ ስም በሐዋርያት ስም እፍኝ ጥሬና ቀዝቃዛ ጽዋ ውኃ የሰጠ ሁሉ ነቢዩ ጻድቁ ሰማዕቱ ሐዋርያው የሚያገኙትን::



ክብር ይህን ያደረገ እንደሚያገኝ እግዚአብሔር ወልድ ቃል ኪዳን ገብቶአል ይህን ታሳቢ በማድርግ ነው ምዕመናን በነቢይ ስም በጻድቅ ስም በሰማዕት ስም በሐዋርያትና በመላዕክት ስም ወጥተው ወርደው ከእግዚአብሔር ያገኙትን በረከት ለእግዚአብሔር በቤቱ በቤተክርስቲያን ሳይገደዱ የሚያፈሱትና የሚያበረክቱት ይህም በጎ ሥራ ምግባር የዕምነታቸው ውጤት ነው::

3. አባ እለስ ወሃብከኒ እፈቅድ ከመ የሀልው ኀበ ሀሎኩ እነ ምስሌየ አባት ሆይ የሰጠኸኝ እነርሱ ደግሞ ከኔ ጋር ይሆኑ ዘንድ እወዳለሁ:: ሐዮ.ምዕ 17 ቁ.24 ዮሐ.ምዕ 14 ቁ. 1-3 ወ.ዘ.ተ ተመልከት ይህን ቃል የሚለውጥ ማንም ምንም የለም እግዚአብሔር አብ በሀብት ስቦ በረድኤት አቅርቦ በእግዚአብሔር ወልድ በኩል ህይወት እንዲያገኙና በህይወት እንዲኖሩ የተፈቀደላቸው ቅዱሳን ከሞተላቸው አምላክ ከክርስቶስ ጋር በክብር ለዘለዓለም እንዲኖሩ በዚህ ቃል ተፈቅዶላቸውል ተወስኖላቸዋል::
4. ወባህቱ በዝሰ ኢትትፈሁ እስመ አጋንንት ይገንዩ ለክሙ ተ ፈስሁስ ባህቱ እስመ ተጽሕፈ አስማቲክሙ በስማያት ይህ ሲተረጎም አጋንንት ተገዙልን ብላችሁ ደስ አይባለችሁ ነገር ግን ስማችሁ በመንግስተ ሰማያት ስለተ ፃፈ በዚህ ደስ ይበላችሁ ሉቃ.ምዕ 10 ቁ.20 ማቴ.ምዕ 10 ቁ.30 ዮሐ.ምዕ 6 ቁ.36 ታላቁ የተስፋ ቃል ይህ ነው ሰው በእግዚአብሔር ካመነና እግዚአብሔር ያዘዘውን ከፈፀመ ስሙ በልበ ሥላሴ ህያው መዝገብ ይቀረፃል/ይጻፋል/ ለዚህ ዕድልና ሀብት የበቁ ቅዱሳን ሀዋርያትና ሴ ሎቹም የእግዚአብሔር የክርስትና ልጆች ናቸው:: ይህ በልበ ሥላሴ በመንግስተ ሰማይ መጻፍ ታላቅ መታሰቢያና ሀብት ነው:: የማይጠፋ የማይለወጥ ሀብተ ነው ::

የእግዚአብሔርን የማዳን ሥራ እንዲሰሩ በእግዚአብሔር የተመ ረጡና የተሾሙ የተላኩ ነቢያት ሀዋርያት ጻድቃን ሰማዕታት

በአጠቃላይ ቅዱሳን አበው የእግዚአብሔር ታማኝ ምርጦቹ ስለሆኑ እነሱም ሥራቸውም እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ህያው ናቸው ህያው ነው:: ከላይ እንደተገለፀው ለማዳን ሥራው የላካቸው እግዚአብሔር መስክሮላቸዋልና በእነሱ ዘንድ ሞት ማጥፋቱ ይቅርና ስም አጠራሩም የለም:: እኔ የህያዋን አምላክ ነኝ እንጂ የሙታን አምላክ አይደለሁም ሲል እግዚአብሔር ወልድ መስክሮአልና ማቴ ምዕ 22 ቁ.31-32 ሄኖክ ምዕ 9ቁ.20 ተመልከት

ማንም በእግዚአብሔር አማኝ የሆነ ሰው የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል የማይጠፋና የማይለወጥ ህያው ቃል መሆኑን በእርግጠኝነት መቀበልና ማመን አለበት ሕዝ.ምዕ 12 ቁ.25

## ምዕራፍ 8

## የጽሑፉ ማጠቃለያ መልዕክት

1. እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውን ነፍስና ሥጋን ተዋህዶ ሰው ሆኖ በሐዲስ ኪዳን መጽሐፍ ሲጾም ሲጸልይ ሲያማልድ ይታያል ይነበባልም ይህ የድርጊት አፈጻጸም ይህን ሥራ እንዲሰሩ ለመረጣቸው ቅዱሳን ሀዋርያት ለማስተማር ለማስገንዘብ እንጂ እርሱ በጾሙ በጸሎቱ በምልጃው የተጠቀመበት አይደለም:: ምክንያቱም ምንም የማያስፈልገው የባህርይ አምላክ ነውና ነው ዮሐ.ምዕ 1 ቁ.1-3 እና ሮሜ ምዕ 9 ቁ.5 1ኛ መል ምዕ 5ቁ.20
2. የእግዚአብሔር ወልድ ሰው የመሆን ምስጢር ያልገባቸው መናፍቃን ኢየሱስ ጌታ ነው ያማልደናል ሲሉ ይስማል ተሳስተዋል ጌትነቱ የባህርይ ነውና እንዳለ ሆኖ ያማልደናል የሚለው ቃል ግን የተሳሳተ አመለካከት ነው ከማነው የሚያማልደው ከእግዚአብሔር ነው? እርሱ ማን ሆኖ እግዚአብሔር አይደለምን? ኢየሱስ እግዚአብሔር ካልሆነማ ድኅነት አልተፈጸመም ማለት ነዋ? የሰው ደም ሰውን አያነጻም ሀቁና እውነቱ ግን ከላይ በቀረበው ማስረጃ



መሰረት ኢየሱስ አምላክ ነው:: ምልጃንና ዕርቅን ይቀበላል እንጂ አያማልድም:: አያስታርቅም የማማለድንና የማስታረቅን ሥራ ለቅዱሳን አበው ለነቢያት ለሐዋርያት ላጻድቃንና ለስማዕታት ለቤተክርስቲያን አስረክቧል:: እውነቱ ይህ ብቻ ነው ዮሐ ምዕ.14 ቁ14 ማቴ ምዕ 7 ቁ.7-8 ሉቃ.ምዕ 11 ቁ.9-10 ማር.ምዕ 11 ቁ.22 ወ.ዘ.ተ ተመልከት ከዚህ የወጣ መንገድ የስህተት መንገድ ነው:::

3. በአዳምና በሔዋን ለእግዚአብሔር ባለመታዘዝ በሰው ዘር ሁሉ የደረሰው መርገምና የኃጢአት ውርስ ዛሬም እግዚአብሔር ወልድ ሰውን ከመርገምና ከፍዳ ለማዳን ሰው ከሆነ በኋላ የአዳምና የሄዋን የኃአጢአት ውርስ አለ ብለው የሚናገሩና የሚጽፉ ሰዎች አልታጡም:: ይህን የሚሉ ሰዎች የአዲስ ኪዳንን መልእክት ህይወት ትርጉሙን የተገነዘቡት አይመስለኝም:: እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው የሆነው እኮ ይህን የውርስ ኃጢአትና መርገም ለመደምሰስ ነው:: ኤፌ.ምዕ.2 ቁ.15-22 ቆላ.ምዕ.2 ቁ.14-15 ወ.ዘ.ተ ተመልከት::

እግዚአብሔር ወልድ በባህርይ አባቱ በአብ በባህርይ ህይወቱ በመንፈስ ቅዱስና በራሱም ፈቃድ በቅድስት ድንግል ማርያም ማኅፀን ሲፀነስ በጀመረው የቤዛነት ሥራና በዕለተ ዓርብ በመስቀል ላይ በፈጸመው መስዋዕትነትና በዕለተ እሁድ ሙስና መቃብርን በማጥፋት ትንሳኤ ሙታን በማወጅ እስከ እርገቱ ድረስ ባደረገው የማዳን ሥራ በሰው ልጆች ላይ በውርስ ተላልፎ የነበረው መርገምና ኃጢአት ተደምስሶአል:: ከስቅለትና ከትንሳኤ በኋላ በማንም ሰው ላይ የአዳምና የሄዋን በደል የኃጢአት ውርስ የለም ፋይሉ ተዘግቶአል:: ማንም ሰው ከሞተ በኋላ እንደሥራው በእግዚአብሔር የሚፈረድበት ባለማመኑ ባለመጠመቁና ለድኅነት ማኅተም ከአምላኩ የተሰጠውን መስዋዕት ሥጋ ወደሙ ባለመቀበሉና ለህገ ወንጌል ባለመታዘዙ እንጂ አዳምና ሔዋን በሰሩት ኃጢአት አይፈረድበትም ምክንያቱም እግዚአብሔር ለሁሉም እንደሥራው ዋጋውን

እከፍለዋለሁ ብሎአልና ነው:: ራዕ. ምዕ. 22 ቁ.12-13 ራዕ.20 ቁ.13 ዮሐ.ምዕ 5 ቁ.28-9 ሞቱም በምልዓት ነውና:: የኃጢአት ውርስ የለም::

4. ስለቅዱሳን መናፍቃን ሲናገሩ በህይወተ ሥጋ በነበሩ ጊዜ ያማልዱ እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል:: አሁን ግን ሞተዋል ጠፍተዋል አያውቁም አያማልዱም በማለት በእየአደባባይና በእየመጋዘኑ ሲደሰኩሩ ይሰማል:: ተሳስተዋል ቅዱሳንን አያውቋቸውም ቅዱሳን በታ ጊዜ ለውጡ እንጂ አልሞቱም አልጠፉም ህያዋን ናቸው ሥጋው እረፍት ነው ያገኙት ዛሬ በዘመነ ሥጋዌ ሰንኳን በቅዱሳን በማንም ላይ ሞት የለም:: ሞት በክርስቶስ ተሸንፏል:: ሞት ዛሬ ወደ ቀጣይ ህይወት መተላለፊያ መንገድ የሥጋ እ ረፍት ነው:: ስለሆነም ቅዱሳን ከሞቱ በኋላ አያማልዱም አይጸልዩም ማለት ፍጹም ስህተት ነው:: በአጸደ ነፍስ በገነት ለሰው ልጆች እየጸለዩ ነው ያሉት ምክንያቱም ክርስቶስ እነሆ እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁሉ ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ በማለት ቃለ ገብቶላቸዋልና ነው:: ማቴ.ምዕ.28 ቁ. 20 ነገ.ኀል.ምዕ13 ቁ. 20-21

5. በሀብተ ክህነት ኃይልና ሥልጣን በክርስቶስ አምላክነት በማመን በጥምቀት በቅዱስ ቁርባን በንስሐ ተጠቅሞ በህግና በሥርዓት ካልኖሩ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት የማይቻል መሆኑን ክርስቶስ አረጋግጦአል:: ዮሐ.ምዕ.6 ቁ .47 የሐ.ምዕ.3 ቁ.3 እና 5 ማቴ.ምዕ.28 ቁ.19-20 ማር.ምዕ.16 ዮሐ.ምዕ.14 ዮሐ.6 ቁ.53-56 ወ.ዘ.ተ ተመልከት የክርስቶስ ውሳኔ የማይቀየር መሆንም በውል ተገንዘብ:: ሰማይና ምድር ያልፋል ቃሌ ግን አያልፍም ብሎአልና::

6. እግዚአብሔር በቤቱ በቤተመቅደስ ስማቸው ለዘለዓለም እንዲጠራና የማስታረቅ ሥራ እንዲሰሩ የፈቀደላቸው ቅዱሳንን ከእግዚአብሔር እግዚአብሔርን ከቅዱሳን መለየት የሚቻለው ማንም የለም:: የማስታረቅ ሥራ



እንዲሰሩና ለዘለዓለም ህያዋን ሆነው እንዲኖሩ ቃል ኪዳን ገብቶላቸዋልና የቃል ኪዳን ሰዎች ስለሆኑ ሥራቸውም ስማቸውም ለዘለዓለም አይጠፋም ህያው ነው:: ማቴ.ምዕ 10 ቁ.28-30 ማቴ ምዕ 22 ቁ.31-32 ዮሐ.ምዕ.6 ቁ.47 ኤፌ.ምዕ. 2 ቁ.19-22 ራዕ ምዕ.22 ቁ.3-5 ወ.ዘ.ተ ተመልከቱና ከቅዱሳን የ በረከታቸውና የቃል ኪዳናቸው ተካፋይ እንድትሆኑ በእግዚአብሔር ስም እመክርሃለሁ::

## ማሳሰቢያ:-

ነኪር ነገሩ በእንቲአኪ ሀገረ እግዚአብሔር የተባለች የእግዚአብሔር ወልድ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም የአምላክ እናትነትና የምልጃ አፈጻጸም በዚህ ጽሑፍ ያልተመዘገበው እርሷ የአምላክ እናት ስለሆነችና ከፍጡራን በላይ ከልጇ ከፈጣሪ በታች የፀጋ ማዕከል ስለሆነች እግዚአብሔ ር ቢፈቅድልኝ ስለእርስዋ እራሱን አስችዬ ለመጻፍ ስለአሰብኩ ይኸው እንዲታወቅልኝ ለአንባቢያን በአክብሮት አገልጻለሁ::

## ወስብሐት ለእግዚአብሔር

ከእናቴ ማህፀን ጀምሮ እስከአለሁበት የጊዜ ምዕራፍ ድ ረስ በሥራየና በህይወቴ ያልተለየኝ አምላክ እግዚአብሔር ክብር ምሥጋና ይግባው አሜን::

ቀሲስ ታደሰ አይፎክሩ የሰዋሰወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ኮሌጅ የቲዎሎጂ/ትምህርተ ሃይማኖት/መምህር